## ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ፪ ።

### ምዕራፍ ፩ ።

### ክፍል ፩ ፡ በእንተ ጥብአት ወተወክሎ በክርስቶስ ።

፩ እምጳውሎስ ሐዋርያሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃደ
እግዚአብሔር ወጢሞቴዎስ እኁነ ለቤተ ክርስቲያን
ዘማኅበረ እግዚአብሔር ዘሀገረ ቆሮንቶስ ወለኵሎሙ
ቅዱሳን እለ ሀገረ አካይያ ።

፪ ሰላም ለክሙ ወጸጋ እግዚአብሔር አቡነ ወእግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፫ ይትባረክ እግዚአብሔር አቡሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ
ክርስቶስ አቡሃ ለምሕረት ወአምላክ ለኵላ ትፍሥ
ሕት ።

፬ ዘአስተፍሥሐነ እምኵሉ ሕማምነ ከመ ንክሃል
አስተፍሥሐቶሙ ለኵሎሙ ሕሙማን በውእቱ ፍሥ
ሓነ ዘአስተፍሥሐነ እግዚአብሔር ።

፭ ወበከመ በዝኀ ሕማሙ ለክርስቶስ ላዕሌነ ፡ ከማሁ
ይፈደፍድ ፍሥሐነ በክርስቶስ ።

፮ ወእመኒ ሐመምነ ከመ አንትሙ ትድኀኑ ወትትፈ
ሥሑ ፡ ወእመኒ ተፈሣሕነ ንሕነ ከመ አንትሙ ትት
ፈሥሑ ወትፅንዑ በትዕግሥቱ ለውእቱ ሕማም
ዘበቱ ነሐምም ንሕነሂ ።

፯ ወትውክልትነሂ ጽኑዕ በእንቲአክሙ ወበከመ ዐረይ
ክሙ ሕማመነ ከማሁ ተኀብሩ በፍሥሓነሂ ።

፰ ወኢፈቅድ ታእምሩ አኀዊነ ዘከመ ሐመምነ በእስያ
እስመ ፈድፋደ እምአምጣነ ኃይልነ አመንደቡነ እስከ
ቀበፅናሃ ለሕይወትነ ።

፱ ወአጥባዕነ ለመዊት ከመ ኢንትአመን በርእስነ ዘእን
በለ በእግዚአብሔር ዘያሐይዎሙ ለሙታን ።

፲ ዘአድኀነነ እመጠነዝ ሞት ወዓዲ ኪያሁ ንትአመን
ከመ ያድኅነነ ።

፲፩ እንዘ ትረድኡነ አንትሙኒ በጸሎትክሙ ከመ ንር
ከብ ሞገሰ በጸሎተ ብዙኃን ፡ ወአንትሙኒ ትትአ
ኰቱ በኀበ ሰብእ ።

፲፪ እስመ ዛቲ ይእቲ ትምክሕትነ ወስምዐ ግዕዛንነ በም
ሕረቱ ወበተመይጦቱ ወበጸጋ እግዚአብሔር አንሶስ
ውነ ውስተ ዓለም ወኢኮነ በትምህርተ ሥጋ ወፈድ
ፋደሰ በኀቤክሙ ።

## ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ፪ ።

### ምዕራፍ ፩ ።

### ክፍል ፩ ፡ በጥብአት ክርስቶስን ስለ ማመን ።

በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ፩
ከሆነው ከጳውሎስና ከወንድማችን ከጢሞቴዎስ
በቆሮንቶስ ሀገር ያለችው የእግዚአብሔር ማኅበር
ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያንና በአካይያ ሀገር ላሉት
ቅዱሳን ሁሉ ትድረስ ። ፩ ቆሮ ፩ ፩ ። ቈላ ፩ ፪ ።
ሰላም ለእናንተ ይሁን ፡ የአባታችን የእግዚአብሔር ፪
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ይደረግላችሁ ።
ሮሜ ፩ ፯ ። ፊል ፩ ፪ ።
የምሕረት አባት የደስታ ሁሉ ባለቤት የጌታችን የኢ ፫
የሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር ይመስገን ።
ሮሜ ፲፭ ፭ ። ኤፌ ፩ ፫ ።
እግዚአብሔር ደስ ባሰኘን በዚያው ደስታ ሕሙማንን ፬
ሁሉ ደስ እናሰኛቸው ዘንድ ከመከራችን ሁሉ ደስ
ያሰኘን ። ዘፀ ፴፬ ፮ ። ግ ሐ ፭ ፵፩ ።
ስለ ክርስቶስ የምንቀበለው መከራ በእኛ ላይ እንደ ፭
ፀና መጠን እንዲሁም ደስታችን በክርስቶስ ይበ
ዛል ። መዝ ፴፬ ፰ ። ፺፬ ፲፱ ።
መከራውን ብንቀበልም እናንተ እንድትድኑና ደስ ፮
እንዲላችሁ ነው ደስ ቢለንም እናንተ ደስ እንዲላች
ሁና እኛም በምንቀበለው መከራ በሚያመጣ ትዕግ
ሥት እንድትድኑ ነው ። ምዕ ፬ ፲፭-፲፯ ።
ስለ እናንተ ያለን ተስፋ የፀና ነው ፡ በመከራ ከኛ ፯
ጋራ አንድ እንደ ሆናችሁ ፡ በደስታችን አንድ ትሆ
ናላችሁ ። ሮሜ ፰ ፲፯ ።
ወንድሞቻችን ! በእስያም መከራ እንደተቀበልን ልታ ፰
ውቁ እወዳለሁ ፡ ለሕይወታችን ተስፋ እስክንቈርጥ
ድረስ ከዓቅማችን በላይ እጅግ መከራ አፅንተወ.
ብናልና ። የሐዋ ሥራ ፲፱ ፳፫ ።
ሙታንን በሚያስነሣቸው በእግዚአብሔር እንጂ በራ ፱
ሳችን እንዳንተማመን ለመሞት ቈርጠናልና ። ኤር
፲፯ ፭-፯ ። ዕብ ፲፩ ፲፱ ።
እንዲህ ካለ ሞት ያዳነን እንዲህም እንደሚያድነን ፲
እሱን እናምናለን ። ፩ ሳሙ ፯ ፲፪ ። ፪ ጢሞ ፬ ፲፰ ።
እናንተም በጸሎታችሁ እየረዳችሁን በብዙዎች ፲፩
ጸሎት ባለሟልነትን እናገኝ ዘንድ እናንተም በሰው
ሁሉ ፊት ትመሰገኑ ዘንድ ። ሮሜ ፲፭ ፴ ። ፊልሞ
፳፪ ። ምዕ ፬ ፲፭ ።
በቸርነቱ ወደ ምሕረትም በመመለሱ መመኪያችን ፲፪
የነፃነታችን ምስክርና መመኪያችን ይህች ናትና ፡
በእግዚአብሔር ጸጋ በዚህ ዓለም ተመላለስን ፡ በሥ
ጋዊ ዕውቀት አይደለም ይልቁንም በእናንተ ዘንድ ።

ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ፪ ።

፲፫ እስመ አልቦ ዘንጽሕፍ ኀቤክሙ ዘእንበለ ዘታነብቡ ወዘተአምሩ ወዘይትዓወቀክሙ ወእትአመን ከመ ለዝሉፉ ታእምርዎ ለዝንቱ ።

፲፬ በከመ አእመርክሙኒ እምአሐዱ ገጽ ከመ ንሕነ ምክሕክሙ ፤ ወከማሁ አንትሙሂ ምክሕነ በዕለተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፲፭ ወበዝንቱ ፍሥሐ ተአሚንየ መከርኩ እምጻእ ኀቤክሙ በቀዳሚ ከመ ትርከቡ ጸጋ ምክዕቢተ ።

፲፮ ወእሑር መቄዶንያ ወእምህየ እሠወጥ ኀቤክሙ ወአንትሙ ትፈንዉኒ ለምድረ ይሁዳ ።

፲፯ ወዘንተ እንከ ዘመከርኩ ቦኑ እንጋ ከመ ዓብድ ዘገበርኩ ፤ ወቦኑ ዘእመክር ሕገ ሰብእ እመክር እስመ ይደሉ ይኩን ነገርክሙ እመኒ እወ እወ ፤ ወእመኒ አልቦ አልቦ ።

፲፰ ጻድቅ እግዚአብሔር ወኢኮነ ሐሰተ ቃልነ ወኢተቶስሐ እወ ወአልቦ ።

፲፱ እስመ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንሕነ ሰበክነ ለክሙ ፤ አነ ጳውሎስ ፤ ወስልዋኖስ ወጢሞቴዎስ ኢኮነ እወ ወአልቦ ፤ ዳእሙ እወ ኮነ በእንቲአሁ ።

፳ እስመ ኵሉ ዘአሰፈወ እግዚአብሔር ኮነ እሙነ በክርስቶስ ወበእንተዝ በቱ ወበእንቲአሁ አሚነ ስብሐት ለእግዚአብሔር ንሁብ ።

፳፩ ወእግዚአብሔር ውእቱ ዘያፀንዐነ ምስሌክሙ በአሚን በክርስቶስ ዘበቱ ቀብአነ ወአተበነ ።

፳፪ ወወሀበነ አረቦነ መንፈስ ቅዱስ ውስተ ልብነ ።

፳፫ ወአነ አሰምዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ነፍስየ ከመ በምሒከ ዚአክሙ ኢመጻእኩ ቆሮንቶስ ።

፳፬ ወአኮ ዘናጌብረክሙ ትእመኑ ዳእሙ ንረድአክሙ ለገቢረ ፍሥሓክሙ እስመ በአሚን ቆምክሙ ወአጥባዕክሙ በሃይማኖት ።

ምዕራፍ ፪ ።

## ክፍል ፪ ፡ በእንተ ተናግሮተ ጽድቅ ።

፩ ወዘንተ እንከ መከርኩ በነፍስየ ኢይምጻእ ትኩዝየ ኀቤክሙ ።

፪ ወእመሰ አነ አተክዝኩክሙ መኑ ያስተፌሥሐኒ ዘእንበለ ዘአነ አተከዝክዎ ።

፫ ወዘኒ ዘጸሐፍኩ ለክሙ ከመ መጺእየ ኢይርከበኒ ኀዘን በዘሀለወኒ እትፌሣሕ ተአሚንየ በኵልክሙ ከመ ፍሥሐ ዚአየ ዘኵልክሙ ውእቱ ።

ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ፪ ።

የምንጽፍላችሁ የምታነቡትን የምታውቁትንና የሚረዳችሁን እንጂ ሌላ አይደለም ፡ እስከ መጨረሻው ይህን እንደምትታመኑት እተማመናለሁ ። ፲፫

እኛ መመኪያችሁ መሆናችንን በአንድ ወገን እንደ ዐወቃችሁን መጠን እንዲሁ እናንተም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ቀን መመኪያችን ናችሁ ። ምዕ ፭ ፲፪ ። ፊል ፪ ፲፮ ። ፲፬

ይህንንም ደስታ ተማምኜ ዕጽፍ ድርብ ጸጋ ታገኙ ዘንድ በመጀመርያ ወደ እናንተ እመጣ ዘንድ መከርኩ ። ፩ ቆሮ ፬ ፲፱ ። ፲፭

ወደ መቄዶንያ ሂጄ ወደ እናንተ እንድመለስ እናንተም ወደ ይሁዳ እንድትሸኙኝ ። ሮሜ ፩ ፲፩ ። ፩ ቆሮ ፲፮ ፭ ። ፲፮

እንግዲህ ይህን የመከርኩ በውኑ የሠራሁት እንደ አላዋቂ ሰው ነውን ? የምመክረውስ ለሰው ይምሰል እመክራለሁን ? ነገራችሁ የሆነውን ሆኗል ፡ ያልሆነውን አልሆነም ማለት ይገባል ። ምዕ ፲ ፪ ። ፲፯

እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ፡ የተናገርነው ሐሰት አይደለም እውነትና ሐሰት አልተቀላቀለበትም ። ፲፰

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነውና እኔ ጳውሎስ ስልዋኖስና ጢሞቴዎስ እኛ የሰበክንላችሁ እውነትና ሐሰት አይደለም ስለርሱ ያስተማርነው ትምህርት ሁሉ እውነት ነው እንጂ ። ሉቃ ፩ ፴፭ ። ፲፱

እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ሁሉ በክርስቶስ እውነት ሆኗልና ፡ ስለዚህ በእርሱ አምነን ስለ እውነተኛነቱ ለእግዚአብሔር እውነተኛ ምስጋናን እናቀርባለን ። ኢሳ ፯ ፲፬ ። መዝ ፹፪ ፲፯ ። ራእ ፫ ፲፬ ። ፳

ከእናንተ ጋር በክርስቶስ ለማመን የሚያፀናን እርሱ እግዚአብሔር ነው በክርስቶስ ያከበረን የለየን ። ፳፩

በልባችንም የመንፈስ ቅዱስን ፈለማ ሰጠን ። ምዕ ፭ ፭ ። ሮሜ ፰ ፲፮ ። ፳፪

እኔ ለእናንተ በማዘን ወደ ቆሮንቶስ እንዳልመጣሁ ስለራሴ እግዚአብሔርን ምስክር አደርገዋለሁ ። ፳፫

እንድታምኑ ግድ የምንላችሁ አይደለም ፡ ደስ የሚላችሁን እንድታደርጉ እንረዳችኋለን እንጂ ፡ በሃይማኖት ፀንታችኋል በአመናችሁትም ረግታችኋልና ። ሮሜ ፲፩ ፳ ። ፩ ጴጥ ፭ ፫ ። ፳፬

ምዕራፍ ፪ ።

## ክፍል ፪ ፡ እውነት ስለ መናገር ፬

እንግዲህ አዝኜ ወደ እናንተ እንዳልመጣ በልቤ ይህን መከርኩ ። ምዕ ፲፪ ፳፩ ። ፩

እኔማ ካሳዘንኳችሁ እኔ ካሳዘንኩት በቀር ማን ደስ ያሰኘኛል ? ። ፪

ይህንንም የጻፍኩላችሁ የኔ ደስታ የሁላችሁ እንደ መሆኑ መጠን ደስ እንደሚለኝ በሁላችሁ አምኜ እዚያ መጥቼ ኃዘን እንዳያገኘኝ ነው ። ገላ ፭ ፲ ። ፫

፬ እስመ እምነ ብዙኅ ሕማም ወኀዘነ ልብ ጸሐፍኩ
ለክሙ ዘንተ በብዙኅ አንብዕ ወአኮሰ ከመ ትተክዙ
ዳእሙ ከመ ታእምሩ አፍቅሮትየ ከመ ፈድፋደ አፈ
ቅረክሙ ።
፭ ወዘኒ አተከዘኒ አኮ ኪያየ ባሕቲቶ ዘያቴክዝ ዳእሙ
ኵልክሙ ዘእንበለ አሐዱ ኀብር እምኔክሙ ፣ ወይእ
ዜኒ ኢያከብድ ቃልየ ላዕሌክሙ ።
፮ ተአክሎ ለዘከመዝ ዛቲ ተግሣፅ እንተ ረከቦቶ እም
ብዙኃን ወዓዲ ይደሉ ከመ ትሥረዩ ሎቱ ወታስተ
ፍሥሕዎ ።
፯ ከመ ኢይሠጠም እምብዝኃ ኀዘን ዘከመዝ ።

፰ ወበእንተዝ አስተበቍዐክሙ ታጽንዑ ተፋቅሮ ምስ
ሌሁ ።
፱ ወበእንተዝ ጸሐፍኩ ለክሙ ከመ እእምር ግዕዘክሙ
ለእመሁ በኵሉ ትትኤዘዙኒ አው አልቦ ።
፲ ወእመቦ ዘሠረይክሙ ሎቱ አንሂ ሠረይኩ ምስሌ
ክሙ ፣ ወእመሂቦ ዘኀደግሙ ሎቱ ኀደጉ ለልየ በእ
ንቲአክሙ በገጹ ለክርስቶስ ።
፲፩ ከመ ኢይትዐገለነ ሰይጣን እስመ አኮ ዘንቶስሕ ሕሊ
ናሁ ።
፲፪ ወበጺሕየ ጢሮአዳ ውስተ ትምህርቱ ለክርስቶስ ተከ
ሥተ ሊተ ፍኖተ እግዚአብሔር ።

፲፫ ወኢረከብኩ ዕረፍተ ለነፍስየ እስመ ኢረከብክዎ
ለቲቶ እኁየ ወተፈለጥኩ እምኔሁ ወሖርኩ መቄ
ዶንያ ።
፲፬ አኰት እግዚአብሔር ዘዘልፈ የዐቅበነ በእግዚእነ
ክርስቶስ ወተዐውቀ በላዕሌነ መአዛ አእምሮቱ በኵሉ
በሐውርት ።
፲፭ እስመ መአዛሁ ለክርስቶስ ንሕነ በኀበ እግዚአብሔር
በእንተ እለ ይድኅኑ ወእለሂ ይትኀጐሉ ።
፲፮ እስመቦ እለ ይደልዎሙ መአዛ ሞት ለሞት ፣ ወቦ
እለ ይደልዎሙ መአዛ ሕይወት ለሕይወት ፣ ወመኑ
ዘይደልዎ ዝንቱ ።
፲፯ እስመ ኢኮነ ከመ ብዙኃን እለ ይትሜየንዎ ለቃለ
እግዚአብሔር በካልእ ፣ ዳእሙ በንጽሕ ወከመ ዘመ
ጽአ እምእግዚአብሔር ንነግር በቅድመ እግዚአብ
ሔር በእንተ ክርስቶስ ።

ምራፍዕ ፫ ።

<u>ክፍል ፫ ፣ በእንታ ጽሒፈ መልእክተ</u>

<u>ክርስቶስ ለመእመናን ።</u>

፩ አኀዊነ ነአኀዝኑ ካዕበ ይእዜ ንንግርክሙ ንወ
ድስ ርእሰነ ወቦኑ ዘንፈቅድ ከመ እልክቱ ካልአን
እስከ ንጽሐፍ ኀቤክሙ በእንቲአነ መጽሐፈ አው
ከመ ትጽሐፉ አንትሙ ።



ከብዙ መከራና ከልብ ኃዘን የተነሣ በብዙ ዕንባ ፬
ይህን ጽፌላችኋለሁና ፣ ግን እንድታዝኑ አይደለም ፣
እጅግ በጣም እንደምወዳችሁ መውደዴን እንድታ
ውቁ ነው እንጂ ። ምዕ ፯ ፰-፱ ።
ያሳዘነኝም እኔን ብቻ ያሳዘነኝ አይደለም ፣ ሁላችሁ ፭
ንም እንጂ ፣ ከሙ ከከላችሁ ከጥቂቶቹ በቀር አሁንም
በእናንተ ላይ ሥራት አላከብድም ። ፩ ቆሮ ፭ ፩ ።
እንደዚህ ላለው ሰው ከብዙዎች ያገኘችው ይህች ፮
ተግሣፅ ትበቃዋለች ደግሞም ይቅር ልትሉትና ደስ
ልታሰኙት ይገባል ። ፩ ጢሞ ፭ ፳ ። ገላ ፮ ፩ ።
እንዲህ ካለው ኃዘን ብዛት የተነሣ ተስፋ እንዳይ ፯
ቈርጥ ።
ስለዚህም ከሱ ጋር መፋቀርን ታፀኑ ዘንድ እማልዳ ፰
ችኋለሁ ።
ስለዚህም በሁሉ ትታዘዙኝ እንደሆነ አትታዘዙኝም ፱
እንደሆነ ጠባያችሁን ዐውቀ ዘንድ ጻፍኩላችሁ ።
የማራችሁት ቢኖር እኔም ከእናንተ ጋር እምረዋለሁ ፣ ፲
ይቅር ያላችሁትም ቢኖር እኔ ራሴ ስለ እናንተ በክ
ርስቶስ ፊት ይቅር ብዬዋለሁ ። ሉቃ ፲ ፲፮ ።
ሰይጣን እንዳይበረታብን ሐሳቡን የምንስተው አይ ፲፩
ደለምና ። ሉቃ ፳፪ ፴፩ ። ፩ ጴጥ ፭ ፰ ።
ክርስቶስ ያስተማራት ወንጌልን ለማስተማር ጢሮ ፲፪
አዳ በደረስኩ ጊዜ የእግዚአብሔር መንገድ ተገለጸ
ልኝ ። ግብ ሐዋ ፲፬ ፳፯ ። ፳ ፯ ።
ለሰውነቴ ዕረፍት አላገኘሁም ወንድሜ ቲቶን አላገ ፲፫
ኘሁትምና ከእሱ ተለይቼ ወደ መቄዶንያ ሂጄ ስለ
ነበር ።
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘወትር የሚጠብቀን ፲፬
እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ፣ በያገሩ እሱን የማ
ወቅ ምሥጢር በእኛ ላይ ታወቀ ።
ስለሚድኑትም ስለሚጐዱትም በእግዚአብሔር ዘንድ ፲፭
የክርስቶስ መታወቂያ እኛ ነንና ። ፩ ቆሮ ፩ ፲፰ ።
ሞት ለሚገባው የሞት መታወቂያ ፣ ሕይወት ለሚገ ፲፮
ባው የሕይወት መታወቂያ ሊሆኑ የሚገባቸው እሉና
ይህ የሚገባው ማነው? ። ሉቃ ፪ ፴፬ ።
የእግዚአብሔርን ቃል በሌላ ግብር እንደሚተናኰሉ ፲፯
ብዙዎች አይደለንምና ከተንኰል ርቀን ከእግዚአብ
ሔር እንደመጣ በእግዚአብሔር ፊት የክርስቶስን ነገር
እንናገራለን እንጂ ። ምዕ ፩ ፲፪ ።

ምዕራፍ ፫ ።

<u>ክፍል ፫ ፣ ለምእመናን የክርስቶስን</u>

<u>መልእክት ደብዳቤ ስለ መጻጻፍ ።</u>

ወንድሞቻችን! አሁንስ ደግሞ ራሳችንን እያመሰገን ፩
ልንነግራችሁ እንጀምርን? ወይስ እንደነዚያ እንደ
ሌሎች ስለኛ ደብዳቤ ልንጽፍ ወይም እናንተ ልት
ጽፉልን የምንሻው መሻት አለን? ። ምዕ ፭ ፲፪ ።

፪ ወለነሰ መጽሐፍነ አንትሙ ይእቲ ወጽሕፍት ውስተ
ልብነ ወትትዐወቅ ወያነብባ ኵሉ ሰብእ ።

፫ ወየአምሩክሙ ከመ መልእክተ ክርስቶስ አንትሙ
እንተ ተልእክናሃ ንሕነ ወጽሕፍት ይእቲ ፡ ወአኮ
በማየ ሕመት ዘአንበለ በመንፈሰ እግዚአብሔር
ሕያው ወኢኮነ ጽሌ ዘእብን ዘእንበለ ጽሌ ልብ
ዘሥጋ ።
፬ ወብነ ብሕቱ ከመዝ ተስፋ በኀበ እግዚአብሔር በእ
ንተ ክርስቶስ ።
፭ ወኢይደልወነ ነሐሊ ለሊነ ለርእስነ ወኢምንተኒ ።
፮ እስመ እምኀበ እግዚአብሔር ኃይልነ ዘረሰየነ ላእ
ካነ ለሐዲስ ሕግ ፡ ወአኮ በሕገ መጽሐፍ አላ በሕገ
መንፈስ እስመ መጽሐፍ ይቀትል ወመንፈስ የሐዩ ።

፯ ወሶበ ለእንቲአከቲ መልእክተ ሞት እንተ ተጽሕፈት
በእብን ተገብረ ላቲ ስብሐት እስከ ኢይክሉ ደቂቀ
እስራኤል ነጽሮተ ገጸ ለሙሴ በእንተ ስብሐተ ገጹ
ኀላፊ ።
፰ እፎ እንከ ይትገበር ፈድፋደ ስብሐት ለመልእክተ
መንፈስ ቅዱስ ።
፱ ሶበ ለመልእክት እንተ ታኬንን ወታሐስብ ተገብረ
ላቲ ስብሐት ብዙኅ ፡ ሚመጠን ፈድፋደ መልእክተ
ጽድቅ ትሴባሕ ወትከብር ።
፲ እስከ ትከውን እንተ ተሰብሐት ከመ ዘኢተሰብሐት
ሶበ ያስተዓርይዋ ለዝንቱ ስብሐት ዐቢይ ።
፲፩ ወሶበ ኀላፊ ዘይሰዐር ረከበ ስብሐተ ፡ እፎ ፈድፋደ
ዘይነብር ይረክብ ቀዋሚ ስብሐተ ።
፲፪ ወእንዘ ብነ መጠነዝ ተስፋ ርቱዕ ንቀረብ በገጽ ገሃድ ።

፲፫ ወአኮ ከመ ሙሴ ዘይገለብብ ገጾ ከመ ኢይርአይዎ
ደቂቀ እስራኤል ።
፲፬ ወባሕቱ ተጸለለ ልቦሙ እስከ ይእዜ እስመ ውእቱ
ግላ ነበረ ውስተ ሕግ ብሉይ አምጣነ ተነበ ወኢተ
ከሥተ እስከ አዕረፆ ክርስቶስ ።

፲፭ ወእስከ ዮም ሶበ ያነብቡ ኦሪተ ሙሴ ይገልዎሙ
ልቦሙ ።
፲፮ ወአምከመ ተመይጡ ኀበ እግዚአብሔር የአትት
ውእቱ ግላ እምኔሆሙ ።
፲፯ እስመ እግዚአብሔር መንፈስ ውእቱ ወኀበ ሀሎ
መንፈሰ እግዚአብሔር ሀየ ሀሎ ግዕዛን ።
፲፰ ወንሕነሰ ኵልነ ከሢተነ ገጸነ ንነጽር ስብሐተ እግዚ
አብሔር ከመ ዘበመጽሔት ወንትመሰል በአርአያ
ዚአሁ ከመ ንበእ እምክብር ውስተ ክብር በከመ
ይሁበነ እግዚአብሔር መንፈሱ ።

ለእኛስ ደብዳቤያችን እናንተ ናችሁ ፡ በልባችንም ፪
የተጻፈች መሆኑ ይታወቃል ፡ ሰውም ሁሉ ያነበ
ታል ። ፩ ቆሮ ፱ ፪ ።
እናንተ የተላክናት የክርስቶስ መልእክት እንደሆና ፫
ችሁ ያውቋችኋል ተጽፋለች መጻፏም በቀለም ውኃ
አይደለም ሕያው በሚሆን በእግዚአብሔር መንፈስ
ነው እንጂ ፡ በድንጋይ ሠሌዳም አይደለም በሰው
ልብ ሠሌዳነት ነው እንጂ ።
ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ክርስቶስን ስለ አገለገልን ፬
እንዲህ ያለ ተስፋ አለን ። ዮሐ ፲፬ ፮ ።
እኛም ለራሳችን ምንም ምን ልናስብ አይገባንም ። ፭
ለአዲስ ሕግ አገልጋዮች ያደረገን ኃይላችን ከእግዚ ፮
አብሔር ስለ ሆነ ነውና በመጽሐፍ ሕግ አይደለም
በመንፈስ ሕግ እንጂ ፡ መጽሐፍ ይገድላል ፡ ሰው
ቀት ግን ያድናልና ። ሮሜ ፯ ፮ ። ዮሐ ፮ ፷፫ ።
ስለ ኃላፊ የፊቱ ብርሃን የእስራኤል ልጆች የሙሴን ፯
ፊት ማየት እስኪሳናቸው ድረስ በዚያች በድንጋይ
ላይ ለተጻፈችው ለሞት መልእክት ክብር ከተደረገ
ላት ። ዘፀአ ፴፬ ፴ ።
ለመንፈስ ቅዱስ መልእክትማ ምንኛ እጅግ ክብር ፰
ሊደረግ ይገባ ይሆን ! ። ገላ ፫ ፪ ።
ኃጢአትን ለምታስቈጥርና ለምታስፈርድ ለዚያች ፱
ብዙ ክብር ከተደረገላት የጽድቅ መልእክትማ ምን
ያህል ትከበር ትመሰገን ይሆን ! ። ሮሜ ፩ ፲፯ ።
በዚህ ከፍተኛ ክብር በነጻጸሯት ጊዜ የከበረችው ፲
ያልከበረች እስክትሆን ድረስ ።
የሚያልፈው የሚጠፋው ክብር ካገኘ የማያልፈውማ ፲፩
እንዴት እጅግ ክብር ያገኝ ይሆን ! ።
ይህን ያህል ተስፋ ካለን በግልዋ በፊት ለፊት ልንቀ ፲፪
ርብ ይገባል ።
የእስራኤል ልጆች እንዳያዩት ፊቱን ይሸፍን እንደነ ፲፫
በረው እንደ ሙሴ አይደለም ። ዘፀ ፴፬ ፴፫-፴፭ ።
ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ ልባቸው ተሸፍኗል ያ መሸ ፲፬
ፈኛ ብሉይ ኪዳን በተነበበ ዘመን ሕግ ፀንቶ ኑሯ
ልና ክርስቶስም እስኪያሳልፈው ድረስ አልተገለጠ
ምና ። ሮሜ ፲፩ ፳፭ ።
እስከ ዛሬም የሙሴን ሕግ ሲያነቡ ልቡናቸውን ይሸ ፲፭
ፍናቸዋል ።
ወደ እግዚአብሔር በተመለሱ ጊዜ ግን ያ መሸፈኛ ፲፮
ከእነሱ ይርቅ ነበር ። ሮሜ ፲፩ ፳፫-፳፮ ።
እግዚአብሔር መንፈስ ነውና የእግዚአብሔር መን ፲፯
ፈስ ካለ ዘንድ ከዚያ ነፃነት አለ ። ዮሐ ፬ ፳፬ ።
እኛ ሁላችን ግን ፊታችንን ገልጠን ፊቱን በመስተ ፲፰
ዋት እንደሚያይ ሰው የእግዚአብሔርን ክብር እንደ
እግዚአብሔር ልጅነትን እንደሚሰጠን መጠን ከክ
ብር ወደ ክብር እንገባ ዘንድ እሱን እንምሰል ።

## ምዕራፍ ፬ ።

### ክፍል ፩ ፡ በእንተ ትምህርተ ክርስቶስ ።

፩ ወበእንተ ዝንቱ እስመ ብነ ዝንቱ መልእክት በከመ
ምሕረቱ ዘጸገወነ ኢንትሀከይ ወኢንትቄጣዕ ።
፪ አላ ንኀድጎ ለምግባረ ኀፍረት ዘኀቡእ ወኢንሑር
በትምይንት ወኢንትመየኖ ለቃለ እግዚአብሔር ወና
ቅም ርእሰነ በጽድቅ ገሃደ እንበይነ ግዕዘ ኵሉ ሰብእ
በቅድመ እግዚአብሔር ።
፫ ወእመኒ ክዱን ትምህርትነ ክዱን ውእቱ ለሕርቱማን
ወለንፉቃን በዝንቱ ዓለም ።
፬ እስመ ጸለሎሙ ልበሙ እግዚአብሔር አምላክ ዘለ
ዓለም ከመ ኢይርአዩ ብርሃነ ትምህርተ ስብሐተ ክር
ስቶስ ዘውእቱ አርአያሁ ለእግዚአብሔር ።
፭ ወአኮ ለርእስነ ዘንሰብክ ዘእንበለ ለእግዚአብሔር
በእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ወለከሙሰ አቅነ
ይነ ርእሰነ በእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፮ እስመ እግዚአብሔር ዘይቤ ይሥርቅ ብርሃን ውስተ
ጽልመት ውእቱ አብርሃ ውስተ ልብነ ብርሃነ አእ
ምሮ ስብሐቲሁ በገጹ ለኢየሱስ ክርስቶስ ።

### ክፍል ፪ ፡ በእንተ ትንሣኤ ሙታን ።

፯ ወብነ ዝንቱ መዝገብ ውስተ ንዋየ ልሕኵት ከመ
ይኩን ዕበየ ኃይል ዘእምኀበ እግዚአብሔር ወአኮ
ዘእምኀቤነ ።
፰ እንዘ በኵሉ ነሐምም ኢንትመነደብ ንትሜነንዊ
ወኢነኃሥር ።
፱ ንሰደድዊ ወኢትገደፍ ፡ ንዌዐርዊ ወኢንትኀጐል ።

፲ ወዘልፈ ንፀውር ሞቶ ለክርስቶስ በሥጋነ ከመ ይት
ዐወቅ ሕይወቱ ለክርስቶስ በላዕለ ዝንቱ ነፍስትነ
መዋቲ ።
፲፩ እስመ ንሕነ ዘነሐዩ ወትረ ንትሜጦ ለሞት በእንተ
ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ሕይወቱኒ ለኢየሱስ ይት
ዐወቅ በላዕለ ነፍስትነ መዋቲ ።

፲፪ ወይእዜሰ ጸንዐ በላዕሌነ ሞት እንዘ ሕይወት ኀቤነ ።

፲፫ ወብነ አሐዱ መንፈስ ዘሃይማኖት በከመ ይቤ መጽ
ሐፍ አመንኩ በዘነበብኩ ወንሕነኒ አመነ በዘነበብነ ።

፲፬ ወነአምር ከመ ዘአንሥአ ለኢየሱስ እግዚእነ ያነሥ
አነ ኪያነኒ ምስሌሁ ወያቀውመነ ምስሌክሙ ኀቤሁ ።

፲፭ እስመ ኵሉ በእንቲአክሙ ከመ ትፈድፍድ ጸጋሁ
በላዕለ ብዙኃን ወይብዛኅ አኰቴቱ ለስብሐተ እግ
ዚአብሔር ።

## ምዕራፍ ፬ ።

### ክፍል ፩ ፡ ስለ ክርስቶስ ትምህርት ።

እንደ ቸርነቱ የሰጠን ይህ መልእክት አለንና ስለዚህ ፩
እንሰንፍ አንመረር ። ምዕ ፫ ፮ ። ፩ ቆሮ ፯ ፳፭ ።
በሥዉር የሚሠራውን የኀፍረት ሥራ እንተው ፡ ፪
በተንኰል አንኑር ፡ የእግዚአብሔርን ቃል አንተና
ኰል ፡ ስለ ሰው ሁሉ ሥራ ተገልጠን በእግዚአብሔር
ፊት ራሳችንን በእውነት እናጽና ። ፩ ተሰ ፪ ፭ ።
ትምህርታችን የተሠወረ ቢሆንም በዚህ ዓለም ለሚ ፫
ጠራጠሩና ለማያምኑ የተሠወረ ነው ። ፩ ቆሮ ፩ ፲፰ ።
እግዚአብሔርን በመልክ የሚመስለውን የክርስቶስን ፬
ጌትነት የሚያውቁበትን ብርሃን እንዳያዩ የዘለዓለም
አምላክ እግዚአብሔር ልበቸውን አደንቍሮታልና ።
ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምናስተምረው ፭
ትምህርት ለእግዚአብሔር እንጂ ለራሳችን የምናስ
ተምር አይደለም ፡ ለእናንተ ግን ስለ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ብለን ራሳችንን አስገዛንላችሁ ። ምዕ ፩ ፳፬ ።
"በጨለማ ውስጥ ብርሃን ይውጣ" ያለ እግዚአብሔር ፮
የኢየሱስ ክርስቶስን ፊት በማየት ጌትነቱን የምናው
ቅበትን ብርሃን በልባችን አበራ ። ዘፍ ፩ ፫ ።

### ክፍል ፪ ፡ ስለ ሙታን መነሣት ።

በዚህ በሸክላ ዕቃ ይህ ሀብት አለን ፡ ከእኛ ያይደለ ፯
ከእግዚአብሔር የተገኘ ታላቅ ኃይል ይሆን ዘንድ ።
ምዕ ፭ ፩ ። ፩ ቆሮ ፪ ፭ ።
በሁሉ መከራ ስንቀበል አንጨነቅም እንናቃለን አን ፰
ዋረድም ። ምዕ ፩ ፰ ። ፯ ፭ ።
እንሰደዳለን አንወድቅም ፡ እንጨነቃለን አንጐ ፱
ዳም ። መዝ ፴፯ ፳፬ - ፴፫ ።
የክርስቶስን ሞት ሁለ ጊዜ በሥጋችን እንሸከማለን ፲
በዚህ በመዋቲ ሰውነታችን የክርስቶስ ሕይወት ይገ
ለጥ ዘንድ ። ሮሜ ፰ ፲፯ ።
በሕይወት የምንኖር እኛም እኮ ስለ ኢየሱስ ብለን ፲፩
ተላልፈን ለሞት እንሰጣለን ፡ በመዋቲው ሰውነታ
ችን ላይ የክርስቶስ ሕይወቱ ይታወቅ ዘንድ ። መዝ
፵፬ ፳፫ ።
ኋላ ሕይወት ሳለን ዛሬ ግን በኛ ላይ ሞት ሠለጠነ ፲፪
ብን ። ፩ ቆሮ ፬ ፱ ።
ሃይማኖትን የሚገልጥ አንድ መንፈስ አለን መጽ ፲፫
ሐፍ "በተናገርኩት አመንኩ" እንዳለ እኛም በተና
ገርነው አመን ። መዝ ፻፲፮ ፲ ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያስነሣው እርሱ እኛ ፲፬
ንም ከእርሱ ጋር እንዲያስነሣንና ከእናንተ ጋር
በፊቱ እንዲያቆመን እናውቃለን ። ግብ ሐዋ ፫ ፭ ።
ሁሉ ስለ እናንተ ነውና ጸጋው በብዙዎች ላይ ትበዛ ፲፭
ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር የሚቀርበውም ምስ
ጋና ይበዛ ዘንድ ሮሜ ፭ ፲፭ ።

፲፮ ወበእንተዝ ኢንትቌጣዕ ወኢንትሀከይ እስመ ዘእንተ
አፍኣነ ብእሲ በላዩ ወዘእንተ ውስጥነሰ ይትሔደስ
ኵሎ አሚረ ።
፲፯ እስመ ሕማምነ ዘለሰዓት ቀሊል ክብረ ወስብሐተ
አፈድፋዶ ይገብር ለነ ።
፲፰ እስመ ኢንሴፎ ዘያስተርኢ አላ ዘኢያስተርኢ እስመ
ዘያስተርኢ ዓለም ኃላፊ ውእቱ ፡ ወዘሰ ኢያስተርኢ
ቀዋሚ እስከ ለዓለም ውእቱ ።

ምዕራፍ ፭ ።

<u>ክፍል ፯ ፡ በእንተ ዘብነ ተስፋ ሕይወት በሰማያት ።</u>

፩ ወነአምር ከመ ለእመሂ ተነሥተ ቤተ ማኅደርነ ዘበ
ምድር ዘውእቱ ሥጋ ፡ ብነ ሕንፃ በኀበ እግዚአብሔር
ዘበሰማያት ዘኢገብሮ እደ ሰብእ ።

፪ ወኪያሁ ንሴፎ ንልበስ ቤተነ ዘውስተ ሰማያት ዘበ
እንቲአሁ ንሠርሕ ።

፫ ወእምከመ ለበስናሁ ኢክነ ዘንትረከብ ዕራቃቲነ ።

፬ እስመ እንዘሂ ሀለውነ ውስተ ዝንቱ ቤት ነኀዝን
ፈድፋደ እምክበደ ዚአሁ ወኢንፈቅድ ንሰለብ ዘእ
ንበለ ከመ ንልበስ ካልአ መልዕልቴሁ ከመ ይሰጠም
መዋቲ በሕይወት ።
፭ ወውእቱ እግዚአብሔር ይረድአነ በዝንቱ ዘወሀበነ
ዓረበነ መንፈስ ቅዱስ ውስተ ልብነ ።
፮ ተአመኑ እንከ ወአጥብዑ በኵሉ ጊዜ ወተአምሩ
እንከ ከመ እንግዳ አንትሙ ውስተ ዝንቱ ሥጋ ወት
ነግዱ እምነፍስትክሙ ወተሐውሩ ኀበ እግዚእነ ።

፯ እስመ በአሚን ነሐውር ወአኮ በአድልዎ ።

፰ ወፈድፋደ ንትአመን ወንትፌሣሕ እስመ ወፂአነ
እምነፍስትነ ነሐውር ኀቤሁ ወናሠምሮ ለእግዚእነ ።

፱ ወይእዜኒ ናእኵቶ እመኒ ነገድነ ወእመኒ ሀሎነ ሎቱ
ዳእሙ ናድሉ በምግባሪነ ።
፲ እስመ ሀለወነ ኵልነ ንቁም ቅድመ መንበረ ምኵናኑ
ለክርስቶስ ከመ ንትፈደይ በከመ ገበርነ በሥጋነ
እመኒ ሠናየ ወእመኒ እኩየ ።

<u>ክፍል ፰ ፡ በእንተ ከመ ተሐደሰ ኵሉ በክርስቶስ ።</u>

፲፩ ወእንበይነ ዘነአምር ጽድቀ እግዚአብሔር ወፈሪሆቶ
ናአምን ሰብአ ፡ ለእግዚአብሔርሰ ንሕነ ክሡታን
ሎቱ ወንትአመን ከመሂ ንትከሠት በልብክሙ ።



ስለዚህ አንመረር ቸል አንበል በውጭ ያለው ሰው ፲፮
ነታችን ያረጃልና በውስጥ ያለው ሰውነታችን ግን
ዘወትር ይታደሳልና ። ፩ ጴጥ ፬ ፩ ። ኤፌ ፫ ፲፮ ።
ለጥቂት ጊዜ የምንቀበለው መከራችን ክብርን ጌት ፲፯
ነትን አብዝቶ ያመጣልናልና ። ሮሜ ፰ ፲፰ ።
የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ተስፋ አናደርግ ፲፰
ምና ፡ የሚታየው ዓለም ኃላፊ ስለሆነ የማይታየው
ግን ለዘለዓለም ፀንቶ የሚኖር ነው ። ሮሜ ፰ ፳፬ ።

ምዕራፍ ፭ ።

<u>ክፍል ፯ ፡ በሰማያት ስላለን የሕይወት ተስፋ ።</u>

በምድር ያለው ማደሪያ ቤታችን ቢፈርስም ይኸ ፩
ውም ሥጋ ነው ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ የሰው እጅ
ያልሠራው የሰማይ ቤት እንዳለን እናውቃለን ። ኢዮ
፬ ፲፱ ። ዕብ ፲፩ ፲ ። ፪ ጴጥ ፩ ፲፫ - ፲፬ ። ዮሐ ፲፬ ፪ ።
ስለ እሱ የምንደክምለትን በሰማይ ያለ ቤታችንን ፪
እናገኝ ዘንድ እርሱን ተስፋ እናደርጋለን ። ሮሜ
፰ ፳፫ ።
ካገኘነውም በኋላ ዕራቁታችንን የምንገኝ አይደለ ፫
ንም ። ራእ ዮሐ ፫ ፲፰ ።
በዚህ ቤት ውስጥ ሳለንም ከክብደንቱ የተነሣ እጅግ ፬
እናዝናለን ፡ ግን መዋቲ በሕይወት ይለወጥ ዘንድ
በርሱ ላይ ሌላ እንድንለብስ እንጂ ከእሱ እንድን
ለይ አንወድም ። ፩ ቆሮ ፲፭ ፶፫ ።
እርሱ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ፈለማ በሰ ፭
ጠን በዚህ ተስፋ ይረዳናል ። ኢሳ ፳፱ ፳፫ ።
እንግዲህ እመኑ በጊዜው ሁሉ ጨክኑ በዚህ ሥጋ ፮
ሳላችሁ እናንተ እንግዶች እንደሆናችሁ ታውቃላ
ችሁ ከሥጋችሁም ተለይታችሁ ወደ ጌታችን ትሄዳ
ላችሁ ። ዕብ ፲፩ ፲፫ ።
በሐሰት ያይደለ በውነት ፀንተን እንኖራለንና ። ዘዳግ ፯
፲፪ ፱ ። ፩ ቆሮ ፲፫ ፲፪ ። ፩ ጴጥ ፩ ፰ - ፱ ።
ከሥጋችን ተለይተን ወደርሱ እንሄዳለንና ጌታችን ፰
ንም እናገለግለዋለንና ፡ አምነን እጅግ ደስ ይለናል ።
ፊልጵ ፩ ፳፫ ።
አሁንም እናመስግነው ፡ ብንኖርም ብንሞትም በሥ ፱
ራችን ለርሱ ብቻ እናድላ ። መዝ ፴፱ ፲፫ ።
ክፉም በጎም ቢሆን በሥጋችን እንደሠራነው ዋጋች ፲
ንን እናገኝ ዘንድ ሁላችንም ክርስቶስ በሚፈርድበት
ዙፋን ፊት እንቆም ዘንድ አለንና ። ግብ ሐዋ ፲፯
፴፩ ። ሮሜ ፪ ፮ ። ሮሜ ፲፬ ፲ ። ራ ዮሐ ፳፪ ፲፪ ።

<u>ክፍል ፰ ። ሁሉ በክርስቶስ እንደ ታደሰ ።</u>

የእግዚአብሔር ቸርነቱን መፈራቱን ስላወቅን ሰውን ፲፩
እናሳምናለን እኛ ለእግዚአብሔር የተገለጥን ነን ፣
እንዲሁ በልቡናችሁም እንደምንገለጥ እንታመና
ለን ። ኢዮ ፴፩ ፳፫ ።

፲፪ ወአኮ ዘንዌድስ ርእሰነ በዝንቱ በኀቤክሙ ወጻእሙ-
ንሁበክሙ ምክንያተ ትጽንዑ በዘትትሜክሑ ብነ
አንትሙሂ ከማነ ከመ ይኩንክሙ ለኀበ እለ ይትሜ
ክሑ ለገጽ ወአኮ ለልብ ፡፡

፲፫ እስመ ንሕነሰ ለእመሂ ከነ ዓብዳነ ዕበድነ ለእግዚአብ
ሔር ፥ ወእመሂ ከነ ጠቢባነ ጥበብነ ለክሙ ፡፡

፲፬ እስመ ፍቅረ ክርስቶስ ያጌብረነ ናጥብዕ ውስተ ዝንቱ
ሕሊና እስመ አሐዱ ሞተ ቤዛ ኵሉ በዘወድአ ሞተ
ኵሉ ፡፡
፲፭ ውእቱ ሞተ በእንተ ኵሉ ከመ እለሂ የሐይዉ አኮ
ለርእሶሙ ዘየሐይዉ ዘእንበለ ለዝኩ ዘበእንቲአሆሙ
ሞተሂ ወሐይወሂ ፡፡
፲፮ ወይእዜሰ አልቦ ዘነአምሮ በሥጋነ ወእመሂ አእመር
ናሁ ለክርስቶስ በሥጋነ እምይእዜሰ አልቦ ዘነአምሮ
እንከ ፡፡
፲፯ ወይእዜሰ በክርስቶስ ተሐደሰ ኵሉ ዘኮነ ወኀለፈ ዘት
ካት ፡፡
፲፰ ወናሁ ኮነ ኵሉ ሐዲሰ እምኀበ እግዚአብሔር ዘአቅ
ረበነ ኀቤሁ በክርስቶስ ወወሀበነ መልእክተ ሥም
ረቱ ፡፡
፲፱ እስመ ተዋለጠ እግዚአብሔር ዓለመ በክርስቶስ አና
ሕሲዮ ኃጢአቶሙ ወኢነጺሮ ጌጋዮሙ ወረሰየ ላዕ
ሌነ ቃለ ሥምረቱ ወወሀበነ መልእክተ ሣህሉ ፡፡

፳ ወንሕነሰ ንተነብል በአምሳለ ክርስቶስ ወይሁበክሙ
እግዚአብሔር ፍሥሓ በላዕሌነ ወንስእለክሙ በክር
ስቶስ ከመ ታሥምርዎ ለእግዚአብሔር ፡፡
፳፩ እስመ ዘኢየአምር ኃጢአተ ረሰየ ርእሰ ኃጥአ በእን
ቲአነ ከመ ኪያነ ያጽድቀነ ለእግዚአብሔር ፡፡

ምዕራፍ ፮ ፡፡

<u>ክፍል ፰ ፥ ዘከመ ይደሉ ተጋድሎ በእንተ ስመ ክርስቶስ ፡፡</u>

፩ ወናስተበቍዕሂ ኀቤክሙ ወንረድእሂ ተወክፉ ለነ
ወኢትረስይዋ ለከንቱ ለጸጋ እግዚአብሔር እንተ
ነሣእክሙ ፡፡
፪ እስመ ከመዝ ይቤ በዕለት ኅሪት እሰምዓከ ወበዕለተ
መድኃኒት እረድአከ ወናሁ ይእዜ ዕለት ኅሪት ፥
ወናሁ ዮም ዕለተ አድኅኖት ፡፡

፫ ዑቁ እንከ ወኢተሀቡ ለመኑሂ ዕቅፍተ ከመ ኢታ
ልስሑ መልእክተክሙ ወኢታንውርዋ ፡፡
፬ ወበኵሉ አርትዑ ርእሰክሙ ወኩኑ ላእካነ ለእግዚ
አብሔር በብዙኀ ትዕግሥት በኵሉ ሕማም ወፃዕር
ወምንዳቤ ፡፡



በዚህም በእናንተ ዘንድ ራሳችንን የምናመሰግን አይ ፲፪
ደለም ከልብ ሳይሆን ለሰው ይምሰል ለሚመኩ
ሰዎች መመለሻ ሊሆናችሁ እናንተም እንደኛ በእኛ
በምትመኩ ገንዘብ ትፀኑ ዘንድ ምክንያት እንሰጣች
ኋለን እንጂ ፡፡ ምዕ ፫ ፩ ፡፡
እኛ ስነፎችም ብንሆንም እኮ ስንፍናችን ለእግዚ ፲፫
አብሔር ብለን ነው ፥ ሊቃቂዎች ብንሆንም አላዋቂ
ነታችን ለእናንተ ነው ፡፡ ምዕ ፲፩ ፩ ፡፡
ሰው ሁሉ ፈጽሞ እንደሞተ አንዱ ስለ ሁሉ ቤዛ ፲፬
ሙቷልና ፤ የክርስቶስ ፍቅር በዚህ አሳብ እንድ
ንፀና ያደርገናል ፡፡ ኢሳ ፶፫ ፮ ፡፡ ማቴ ፳ ፳፰ ፡፡
በሕይወት የሚኖሩትም ስለ እነርሱ ሙቶ የተነሣውን ፲፭
ለማገልገል እንጂ ራሳቸውን ለማገልገል እንዳይኖሩ
እርሱ ስለ ሁሉ ሞተ ፡፡ ፩ ጢሞ ፪ ፮ ፡፡ ፩ ጴጥ ፬ ፪ ፡፡
ዛሬ ግን በሥጋ የምናውቀው የለም ፥ ክርስቶስን ፲፮
በሥጋ ብናውቀውም እንግዲህ ወዲህ በሥጋ የምና
ውቀው አይደለም ፡፡ ማቴ ፲፪ ፶ ፡፡ ዮሐ ፮ ፳፫ ፡፡
አሁንስ በክርስቶስ የሆነው ሁሉ ታድሷል ፈተኛ ፲፯
ውም አልፏል ፡፡ ኢሳ ፵፫ ፲፱ ፡፡ ራእ ዮሐ ፳፩ ፭ ፡፡
በክርስቶስ ወደርሱ ካቀረበንና የማስታረቁን መልእ ፲፰
ክት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ሐዲስ ሆነ ፡፡
ሮሜ ፭ ፲ ፡፡
በደላቸውን ሳይመለከት ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎ ፲፱
እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለሙን ዋጅቷልና የዕር
ቁንም ቃል በኛ አደረገ የይቅርታውንም መልእክት
ሰጠን ፡፡ ሮሜ ፫ ፳፬ - ፳፭ ፡፡ ቈላ ፩ ፲፱ - ፳ ፡፡
እኛስ በክርስቶስ አምሳል እንማልዳለን እግዚአብ ፳
ሔርም በእኛ ደስታን ይሰጣችኋል ፥ እግዚአብሔርን
ታገለግሉት ዘንድ በክርስቶስ ስም እንለምናችኋለን ፡፡
ኃጢአት የሌለበት እርሱ እኛን የእግዚአብሔር ቤተ ፳፩
ሰብእ ለመሆን ያጸድቀን ዘንድ ስለ እኛ ራሱን ኃጥእ
አሰኝቷልና ፡፡ ፩ ጴጥ ፪ ፳፪ ፡፡ ዕብ ፱ ፲፭ ፡፡ ገላ ፫ ፲፫ ፡፡

ምዕራፍ ፮ ፡፡

<u>ክፍል ፰ ፥ ለክርስቶስ ስም ተጋድሎ እንደሚገባ ፡፡</u>

እንማልዳችኋለን እንረዳችሁም አለን ፥ ነገራችንን ፩
ተቀበሉን የተቀበላችኋትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ለከ
ንቱ አታድርጓት ፡፡ ምዕ ፩ ፳፬ ፡፡ ፭ ፬ ፡፡ ዕብ ፲፪ ፲፭ ፡፡
"በተመረጠችው ቀን እሰማሃለሁ በማድንበትም ቀን ፪
እረዳሃለሁ„ ተብሎ ተጽፏልና እነሆ የተመረጠችው
ቀን ዛሬ ናት ፥ ድኅነት የሚገባትም ቀን ዛሬ ናት ፡፡
ኢሳ ፵፱ ፰ ፡፡ ሉቃ ፬ ፲፱ - ፳ ፡፡
እንግዲህ ተጠንቀቁ መልእክታችሁን እንዳታስነው ፫
ሩና እንዳታስነቅፉ ለማንም ለማን መሰናክል አትሁኑ፤
ራሳችሁን በሁሉ የቀና አድርጉ ለእግዚአብሔር ፬
አገልጋዮች ሁኑ ፥ በፍጹም ትዕግሥት በመታመም
በመጨነቅ በመከራ ፡፡ ምዕ ፬ ፪ ፡፡

| ፩፻፳፮ | ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ፪ ። | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ፪ ። | |
|---|---|---|---|
| ፭ | ወበተቀሥፎ ወበትሞቅሖ ወበሥራሕ ወበትህውክ በትጋሀ ወበጾም ። | በመገረፍ በመታሠር በመድከም በመታወክ በመትጋት በመጾም ። ምዕ ፲፩ ፳፫ - ፳፯ ። | ፭ |
| ፮ | በንጽሕ ወበአእምሮ በምክር ወበተዓግሦ በምሒር ወበመንፈስ ቅዱስ በፍቅር ዘእንበለ አድልዎ ። | በንጽሕና ፣ በዕውቀት ፣ በምክር ፣ በመታገሥ ፣ በመራራት ፣ በንጹሕ ልብ ፣ ያለማድላት ፍቅር ። ፩ ጢሞ ፬ ፲፪ ። | ፮ |
| ፯ | በነገረ ጽድቅ ዘእንበለ ኑፋቄ በኃይለ እግዚአብሔር ወወልታ ጽድቅ ዘእምየማን ወዘእምፀጋም ። | ጥርጥር በሌለው ሃይማኖት በእግዚአብሔር ኃይል ከቀኝ ከግራ ከሚመጣው የጽድቅ ጋሻ የሚሆናችሁን የእግዚአብሔርን ኃይል ተደግፉችሁ ። ፩ ቆሮ ፪ ፬ ። | ፯ |
| ፰ | በክብር ወበኃሣር በምድኅር ወበመርገም ከመ ኃጥአን ወጻድቃን ። | ቢያከብሯችሁም ቢያዋርዷችሁም ቢመርቋችሁም ቢረግሟችሁም ኃጢአተኞች ቢያስመስሏችሁ እንደ ጻድቃንም ቢያደርጓችሁ ። | ፰ |
| ፱ | ከመ እለ ኢየአምርዎሙ ወዕዉቃን ከመ ዓብዳን ፣ ወጠቢባን ከመ ምውታን ፣ ሕያዋን ከመ ምንስዋን ፣ ወኢቅቱላን ከመ ነዳያን ። | እንደማያውቋቸው እንደሚያውቋቸውም ቢያደርጓችሁ እንደ ዐላዋቆች ፣ እንደ ዐዋቂዎች ቢያደርጓችሁ እንደ ሙታን እንደ ሕያዋን ቢቈጥሯችሁ ድል እንደ ተነሡ እንዳልተነሡ ቢያደርጓችሁ ። መዝ ፻፲፰ ፲፰ ። | ፱ |
| ፲ | ከመ ትኩዛን ወከመሂ ዘልፈ ትትፌሥሑ ከመ ነዳያን ወብዙኃነ ታብዕሉ ከመ ዘአልብክሙ ወኢምንተኒ ወኵሉ ውስተ እዴክሙ ። | እንደታምዝኑ ወይም ዘወትር ደስ እንደሚላችሁ ቢያደርጓችሁ ወይም እንደ ደኸያችሁ ብዙዎችን እንደ ምታበለጽጉ ምንም ምን እንደሌላችሁ ፣ ወይም ሁሉ እንዳለ ቢያደርጓችሁ በዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን አገልግሉ ። | ፲ |
| ፲፩ | አፉነ ክሡት ለክሙ ኦ ሰብአ ቆሮንቶስ ወርኅብ ልብነ ። | የቆሮንቶስ ሰዎች! ለእናንተ አፋችን የተከፈተ ልባችንም የሰፋ ነው ። | ፲፩ |
| ፲፪ | ወአልብነ ንሂክ እምኔክሙ ወኢላዕሌክሙ እምኔነ አላ ንህክሙ ወተመንደብክሙ ለምሕረትክሙ ። | ከእናንተ የመጣ ኀዘን በኛ ላይ ፣ ከእኛም የመጣ ኀዘን በእናንተ ላይ የለም ፤ ይቅርታን ለመቀበል መከራ ተቀብላችሁ አዝናችኋል እንጂ ። ምዕ ፲፪ ፲፭ ። | ፲፪ |
| ፲፫ | አብለክሙ ከመ ዘለደቂቅየ በእንተ ውእቱ ፍድዩ ዘይደሉ ሊተ ላዕሌክሙ አርኅቡ ሊተ አፍቅሮተክሙ አንትሙኒ ። | ለልጆቼ እንደምናገር እነግራችኋለሁ ፣ ስለዚህ ከእናንተ ሊከፈለኝ የሚገባውን ክፈሉኝ እናንተም ፍቅራችሁን አብዙልኝ ። ፩ ቆሮ ፬ ፲፬ ። | ፲፫ |
| ፲፬ | ወኢትኩኑ ንፉቃነ ኢትሑሩ ውስተ አርዑተ እለ ኢየአምኑ መኑ ዘያስተዓርዮ ለጽድቅ ምስለ ኃጢአት ወመኑ ዘይዴምሮ ለብርሃን ምስለ ጽልመት ። | ተጠራጣሪዎች አትሁኑ ወደማያምኑ ሰዎች ማኅበር አትሂዱ ጽድቅን ከኃጢአት ጋር አንድ የሚያደርጋት ማን ነው ? ብርሃንስ ከጨለማ ጋር የሚቀላቀለው ማነው ? ዘፀአ ፴፬ ፲፮ ። ዘዳግ ፯ ፪ ። ኤፌ ፭ ፲፩ ። | ፲፬ |
| ፲፭ | ወመኑ ዘያኀብሮ ለክርስቶስ ምስለ ቤልሆር ፣ ወመኑ ዘይከፍሎሙ ለመሃይምናን ምስለ ንፉቃን ። | ክርስቶስን ከሰይጣን ጋር አንድ የሚያደርገው ማነው ? ምእመናንንስ ከመናፍቃን ጋር አንድ ወገን የሚያደርጋቸው ማነው ? ። | ፲፭ |
| ፲፮ | ወመኑ ዘይዴምር ታቦተ እግዚአብሔር ውስተ ቤተ ጣዖት ፣ አኮኑ ንሕነ ውእቱ ቤቱ ለእግዚአብሔር ሕያው ፣ በከመ ይቤ እግዚአብሔር እነ አኀድር ኀቤሆሙ ወእንሶሱ ማእከሎሙ ወእከውኖሙ አምላከሙ ወእሙንቱኒ ይከውኑኒ ሕዝብየ ። | የእግዚአብሔርንስ ታቦት በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነው ? የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያዎች እኛ አይደለንምን ? ፣ እግዚአብሔር "እኔ በነርሱ አድራለሁ በመካከላቸው እኖራለሁ ፤ አምላካቸውም እሆናቸዋለሁ" ፣ እነሱም ሕዝቤ ይሆኑኛል እንዳለ ። ዘሌ ፳፮ ፲፪ ። ፩ ቆሮ ፫ ፲፮ ። | ፲፮ |
| ፲፯ | ወበእንተ ዝንቱ ፃኡ እማእከሎሙ ወተፈለጡ ይቤ እግዚአብሔር ፣ ወኢትቅረቡ ኀበ ርኩሳን ወአነ እትዌከፈክሙ ። | ስለዚህ እግዚአብሔር ከመካከላቸው ተለይታችሁ ውጡ ወደ ርኩሳንም አትቅረቡ እኔም በረድኤት እቀበላችኋለሁ አለ ። ኢሳ ፵፰ ፳ ፤ ፶፪ ፲፩ ። | ፲፯ |
| ፲፰ | ወእከውነክሙ አበክሙ ወአንትሙኒ ትከውኑኒ ደቂቀየ ወአዋልድየ ይቤ እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ ። | ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር አባት እሆናችኋለሁ እናንተም ወንዶች ልጆች ፣ ሴቶች ልጆች ትሆኑኛላችሁ አለ ። ኤር ፴፩ ፱ ። | ፲፰ |

## ምዕራፍ ፯ ።

### ክፍል ፱ ፡ በእንተ ዘከመ ይደሉ ተወክፎ አርዳእ ።

፩ ወበእንተ ዘብነ ተስፋ እኅዊነ ናንጽሕ ርእሰነ ወኢና
ግምን ነፍስተነ ወንግበር በዘንትቄደስ በፈሪሃ እግዚ
አብሔር ።

፪ ወይእዜኒ ተአምሩ አኀዊነ ከመ አልቦ ዘአማሰነ ወአ
ልቦ ዘገፋዕነ ወአልቦ ዘተዐገልነ ።

፫ ወአኮ ለአድልዎ ዘእብል እስመ ወዳእኩሂ እቤ ከመ
ምሉእን አንትሙ ውስተ ልብነ ለመዊትኒ ወለሕይ
ወትኒ ።

፬ ወከመዝ ብየ ብዙኅ ሞገስ በኀቤክሙ ወብዙኅ ትም
ክሕትየ በእንቲአክሙ ወፈጸምኩ ፍሥሐየ ወፈድ
ፈደኒ ኃሤትየኒ እምኵሉ ሕማምየ ።

፭ ወበጺሐነ መቄዶንያ ኢረከብነ ወኢአሐተኒ ዕረፍተ
ለነፍስነ ወበኵሉ አሕመሙነ በአፍአኒ ቀትል ወመን
ንሱት ፡ ወበውስጥኒ ፍርሃት ።

፮ ወባሕቱ ውእቱ እግዚአብሔር ዘያስተፌሥሖሙ
ለሕሙማን አስተፍሥሐነ በምጽአቱ ለቲቶ ።

፯ ወአኮ በምጽአቱ ባሕቲቱ ዓዲ በፍሥሐ ዘአስተፍ
ሣሕክምዎ ወዜነወነ አፍቅሮተክሙ ዘከመ ትጽሕቁ
ለነ ወትትቃሐዉ፡ ወሰሚዕየ ዘንተ ጸንዐ ፍሥሐየ
ብክሙ ።

፰ ወእመኒ አተከዝኩክሙ ቀዳሚ በመጽሐፍ ዘጸሐ
ፍኩ ለክሙ ኢያኔስሐኒ ፡ ወእመኒ ነሳሕኩ ናሁ እሬ
እያ ለይእቲ መልእክት እመሂ ለአሐቲ ሰዓት አተከ
ዝኩክሙ ናሁ ይእዜ አትፌሣሕ በእንቲአሃ ብዙኃ ።

፱ ወአኮሰ ውእቱ እስመ ተከዝክሙ ዳእሙ እስመ ተከ
ዝክሙ ከመ ትነሥሑ እስመ እንበይነ እግዚአብሔር
ተከዝክሙ ከመ ኢይትኃጐል አሐዱሂ እምኔክሙ።

፲ እስመ ዘበእንተ እግዚአብሔር ኃዘን ንስሓሁ ለሕይ
ወት ዘለዓለም ይከውን፡ ወትካዘሰ ዘበእንተ ዓለም
ሞተ ያመጽእ ።

፲፩ ወናሁ ውእቱ ትካዝ ዘበእንተ እግዚአብሔር ጻሕቀ
ወቅስተ ወፍርሀተ ወግርማ ወተፋቅሮ ወተቃሕዎ
ፍዳ ገብረ ለክሙ እስከ አቀምክሙ ርእሰክሙ በን
ጽሕ ወበምግባር ከመ ዘኢተአምሩ ወኢምንተኒ ።

፲፪ ወዘኒ ዘጸሐፍኩ ለክሙ አኮ በእንተ ዘገፍዐ ወዘተገ
ፍዐ ዳእሙ ከመ ይትዐወቅ ከመ ጽሕቀሙ በእንቲ
አነ በቅድመ እግዚአብሔር ።

፲፫ ወበእንተዝ ተፈሣሕነ ወዓዲ ፈድፋደ ፍሥሐነ ተፈሣሕነ



## ምዕራፍ ፯ ።

### ክፍል ፰ ፡ ደቀ መዛሙርትን ስለ መቀበል ።

ወንድሞቻችን ! ይህ ተስፋ ያለን ስለሆነ ራሳችንን ፩
እናንፃ ፡ ሰውነታችንን በኃጢአት እናሳድፍ እግዚአ
ብሔርን በመፍራት የምንከብርበትን ሥራ እንሥራ ።
፩ ዮሐ ፫ ፫ ።
አሁንም ወንድሞቻችን! የበደልነው የገፋነውም ያጠ ፪
ፋነውም የቀማነውም እንደሌለ ታውቃላችሁ ። ግብ
ሐዋ ፳ ፴፫ ።
ለሰው ይምሰል የምናገር አይደለም ለሞትም ለሕይወ ፫
ትም ቢሆን እናንተ በልባችን እንዳላችሁ ፈጽሜ
ተናግሬአለሁና ። ምዕ ፯ ፲፩ - ፲፫ ።
በእናንተ ዘንድ እንዲህ ብዙ መወደድ አለኝ ፡ ስለ ፬
እናንተም የምመካበት ብዙ ነው ደስታዬን ፈጸ
ምኩ ደስታዬ ከመከራዬ ሁሉ ይልቅ በዝቶልኛ
ልና ። ፩ ቆሮ ፩ ፬ ። ፊል ፪ ፲፯ ።
ወደ መቄዶንያ በደረስንም ጊዜ ለሰውነታችን ፭
ጥቂት ስንኳ ዕረፍት አላገኘንም ፡ በሁሉ መከራ
አፀኑብን በውጭም ጠብ መጋደል ፡ በውስጥም
ፍርሃት መጨነቅ ነበር ።
ግን ያዘኑትን ደስ የሚያሰኝ እርሱ እግዚአብሔር ፮
በቲቶ መምጣት ደስ አሰኘን ። ዘዳግ ፴፪ ፴፭ ።
በመምጣቱም ብቻ አይደለም ፡ ደስ ባሰኛችሁት ደስ ፯
ታም ነው እንጂ ፡ ለእኛ እንደምትከራከሩና እንደም
ታስቡ ፍቅራችሁን ነግሮናልና ፡ ይህን ሰምቼ ደስታዬ
በእናንተ በዛ ።
መጀመሪያ በጻፍኩላችሁ ደብዳቤ ባሳዝናችሁም ፰
እንኳ አያፀፀተኝም ፡ ብፀፀትም እነሆ ያቺን መልእ
ክት አያታለሁ ፡ ለጥቂት ጊዜ ባሳዝናችሁም እነሆ
አሁን ስለ እርሷ በብዙ ደስ ይለኛል ። ምዕ ፪ ፬ ።
ደስታዬም ስለ አዘናችሁ አይደለም ንስሐ ልት ፱
ገቡ ስለ አዘናችሁ ነው እንጂ፡ ከእናንተ መካከል
አንዱ እንዳይጠፋ ስለ እግዚአብሔር አዝናችኋልና ።
ስለ እግዚአብሔር የሚደረግ ኃዘን ፀፀቱ ለዘለዓለም ፲
ሕይወት ይሆናልና፡ ስለ ዓለም የሚደረግ ኃዘን ግን
ሞትን ያመጣል ። ፪ ሳሙ ፲፪ ፲፫ ። ኤር ፴፩ ፲፰-፳ ።
እነሆ ያ ስለ እግዚአብሔር ያደረጋችሁት ኃዘን ፲፩
ምንም ምን የማታውቁ እስከ መሆን ደርሳችሁ ራሳ
ችሁን በበጎ ሥራና በንጽሕ አስከታፀኑ ድረስ
ትጋትን መቃወምን መፈራራትን መከባበርን መዋ
ደድን መከራከርን ብድራት አደረገላችሁ ። ኤር ፶
፬ - ፭ ። ዘካ ፲፪ ፲ ።
ይህን የጻፍኩላችሁ ስለ በደለና ስለ ተበደለ አይደ ፲፪
ለም በእግዚአብሔር ፊት ስለእኛ እንደተጋችሁ
ይታወቅ ዘንድ ነው እንጂ ።
ስለዚህ ደስ አለን በደስታ ላይ ደስታን ጨመርን ፡ ይል ፲፫

ወፈድፋደሰ በፍሥሓ ቲቶ እስመ አዕረፍክምዋ ለነ
ፍሱ በኀበ ኵልክሙ ።
፲፬ እስመ ኢያስተኀፈርክሙኒ በኵሉ ዘተመከሕኩ ሎቱ
በእንቲአክሙ አማነ ረሰይክሙ ለነ ዘነገርናክሙ ወከ
ማሁ እሙነ ኮነ ።
፲፭ ወፈድፋደ የአኵተክሙ ወይዜከረክሙ ዘከመ ትት
ኤዘዙ ሎቱ ወትትወከፍዎ በፍርሀት ወበረዓድ ።
፲፮ ወእትፌሣሕ በሕቱ እስመ በኵሉ እትአመነክሙ ።

ምዕራፍ ፰ ።

ክፍል ፲ ፡ በእንተ ዘከመ ይደሉ አስተዋጽኦ ።

፩ ወእነግረክሙ አኃዊነ ጸጋ እግዚአብሔር ዘተውህበ
ለቤተ ክርስቲያን ዘመቄዶንያ ።
፪ እስመ እምብዙኅ መከራ ሕማሞሙ ፈድፈደ ፍሥሐ
ሆሙ ወምስለ ዕመቀ ንዴቶሙ ፈድፈደት ፍሥሓ
ብዕሎሙ ።
፫ እስመ ለልየ ሰማዕቶሙ ከመ በአምጣነ ኃይሎሙ
ወዘእንበለ ኃይሎሙሂ ጥቡዓን እሙንቱ ለሊሆሙ ።
፬ ወብዙኀ አስተብቍዑነ በእንተ ሱታፌ መልእክተ
ቅዱሳን ።
፭ ወአኮሂ በከመ ተሐዘብነ እስመ ለሊሆሙ አቅደሙ
በፈቃዶሙ ወመጠዉ ነፍሶሙ ለእግዚአብሔር ።
፮ ወአስተፍሥሐነ ቲቶ ወአስተብቋዕናሁ ከመ ይፈጽም
ለክሙ ጸጋሁ በከመ ወጠነ ።
፯ እስመ ፈድፈድክሙ በኵሉ በሃይማኖት ወበቃል
ወበጥበብ ወበጽሒቅ በኵሉ ዘከነ በኀቤክሙ ወአፍ
ቅሮትክሙ ኪያነ ከማሁ አፈድፍዱ ካዕበ ውስተ
ዛቲ ጸጋ ።
፰ ወአኮ በግብር ዘእብለክሙ ዳእሙ እስመ በ እለ ይጽ
ሕቅዎ ለዝንቱ እምኔክሙ ወናሁ አእመርኩ ጽንዐ
ሃይማኖትክሙ ።
፱ ተአምሩ ጸጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእን
ቲአክሙ እንደየ ርእሶ እንዘ ባዕል ውእቱ ከመ አን
ትሙ ትብዐሉ በንዴተ ዚአሁ ።
፲ ወበዝንቱ አምከርኩክሙ ዘይበቍዐክሙ ወአቅደም
ክሙ ትመጥዉ ነፍሰክሙ እምቀዳሚ ዓም ።
፲፩ ወይእዜሰ ግበሩሂ ወፈጽሙሂ እስመ ፈቂድሂ እምፈ
ቲው ወገቢርሂ እምረኪብ ።
፲፪ ወእምከመሰ ፈቂድ ሀሎ ይትመዘገን በዘይትከሀሎ ፤
ወአኮ በአምጣነ ዘኢይትክሃሎ ።
፲፫ ወአኮ ከመ በዕድ ያዕርፍ ኪያክሙ ዘናጠውቅ ዳእሙ
ተሀልዉ ዕሩየ በዝ መዋዕል ።

ቁንም ቲቶን ደስ ስለ አለው ደስ አለን በሁላችሁ ዘን
ድ ሰውነቱን አሳርፋችኋታልና ። ሮሜ ፲፭ ፴፪ ።
፲፬ ስለ እናንተ በተመካሁበት ሁሉ አላሳፈራችሁኝ
ምና የነገርነውን እውነት አደረጋችሁልን ፤ እንዲል
ነውም እውነት ሆነ ።
፲፭ እንደምትታዘዙለት እየፈራችሁ እየደነገጣችሁ እንደ
ምትቀበሉት እያሰበ እጅግ ያመሰግናችኋል ። ፊል
፪ ፲፪ ፡ ምዕ ፪ ፱ ።
፲፮ በሁሉም እተማመናችኋለሁና ደስ ይለኛል ።

ምዕራፍ ፰ ።

ክፍል ፱ ፡ ማዋጣት እንዲገባ ።

፩ ወንድሞቻችን ! በመቄዶንያ ላለችው ቤተ ክርስቲያን
የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ እነግራችኋ
ለሁ ። ሮሜ ፲፭ ፳፮ ፡ ፩ ቆሮ ፲፮ ፩ ።
፪ በመከራ ብዙ ከመፈተናቸው የተነሣ ደስታቸው
በዝቷልና ፡ እንደ ችግራቸው ዕናት እንስጥ ማለታ
ቸው በዝታለችና ። ማር ፲፪ ፵፬ ።
፫ እነሱ ቢቻላቸው በይቻላቸውም ቈራጦች ለመሆና
ቸው ምስክራቸው እኔ ነኝና ።
፬ የቅዱሳንን አገልግሎት ስለ መሳተፍ መላልሰው ማለ
ዱን ። ምዕ ፱ ፩ ። ግብ ሐዋ ፲፩ ፳፱ ።
፭ እኛ እንዳሰብነው እንኳ አይደለም እነሱ አስቀድመው
በፈቃዳቸው ሰውነታቸውን ለእግዚአብሔር አሳል
ፈው ሰጥተዋልና ። ፩ ሳሙ ፩ ፳፰ ።
፮ ቲቶ ደስ አሰኝቶናልና እንደ ጀመረ ደግነቱን ይፈ
ጽምላችሁ ዘንድ ማለድነው ። ምዕ ፲፪ ፲፰ ።
፯ በፍጹም ሃይማኖት በአነጋገር በእውነት በትጋት
በእናንተ ዘንድ በሆነው ሁሉ ፍጹማን ሆናችኋልና
እኛን እንደወደዳችሁ እንዲሁ ይህችን ስጦታ
አብዙ ። መዝ ፻፲፪ ፱ ። ምሳ ፳፪ ፱ ። ፩ ቆሮ ፩ ፭ ።
፰ በግድ የምላችሁ አይደለም ከእናንተ ለዚህ ሥራ
የሚተጉለት ስላሉ ነው እንጂ ፡ የሃይማኖታችሁን የፍ
ቅራችሁን ዕናት አሁን አወቅሁ ። ፩ ቆሮ ፯ ፮ ።
፱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸርነት ታውቃላችሁ
የባሕርይ ባለጸጋ ሲሆን ስለ እናንተ ራሱን ድኻ አን
ዳሰኘ በእሱ ድኽነት እናንተ ትከብሩ ዘንድ ። ማቴ
፰ ፳ ። ፊል ፪ ፯ - ፮ ።
፲ በዚህም የሚጠቅማችሁን ነገርኋችሁ ከድሮ ዘመን
ጀምሮ ሰውነታችሁን አሳልፋችሁ ልትሰጡ ወዳችሁ
ኋልና ። ምሳ ፲፱ ፲፯ ። ፩ ቆሮ ፯ ፳፭ ።
፲፩ አሁንም ሥሩ ፈጽሙ ልስጥ ማለት ከመሻት ነውና
መስጠትም ከማግኘት ነውና ።
፲፪ ልስጥ ማለት ካለ በሚቻለው ይመሰገናል በማይቻ
ለው መጠን አይደለም ። ምሳ ፫ ፳፰ ። ማር ፲፪ ፵፫
፲፫ ሌላው እንዲያርፍ እናንተን የምናስጨንቅ አይደለም
በዘመኑ ሁሉ በመተካከል እንድትኖሩ ነው እንጂ ።

፲፬ እስመ ተረፈ ዚአክሙ ውስተ ንትጋ እልክቱ ይከ
ውን፡ ወተረፈ ዚአሆሙ ውስተ ዚአክሙ ከመ ይኩን
ሀልዎትክሙ ዕሩየ በኵሉ ።
፲፭ እስመ ከመዝ ይቤ መጽሐፍ ዘበ ብዙኀ ኢያትረፈ
ወዘበ ውኁድ ኢያሕፀፀ ።

ክፍል ፲ወ፩፡ በእንተ አርእዮ ፍቅር ለምእመናን ።

፲፮ አኰት እግዚአብሔር ዘወሀበነ ለነሂ ንጽሐቀ በእንቲ
አክሙ በከመ ይቤ ቲቶ ።
፲፯ እስመ የአኰተክሙ ወተወክፈ ለክሙ ሥላጤክሙ
ወአስተፋጠነ ይምጻእ ኀቤክሙ ጥቡዐ ።
፲፰ ወፈነውነ ምስሌሁ እኁነ ዘንእድዎ ኵሉ አብያተ
ክርስቲያናት በእንተ ትምህርቱ ።
፲፱ ዓዲ ሥዩም ውእቱ ለቤተ ክርስቲያን ወኀቡረ ምስ
ሌነ በዛቲ ጸጋ እንተ ተልእክነ ለስብሐተ እግዚአብ
ሔር ከመ ንትፈሣሕ ።
፳ ወተዐቀብዎ ለዝንቱ ከመ ኢታንውርዋ ለመልእክ
ትክሙ ።
፳፩ ወሠናየ ሐልዩ ለቅድመ እግዚአብሔር ወለቅድመ
ሰብእ ።
፳፪ ወናሁ ፈነውነ ምስሌሆሙ ዓዲ እኁነ ዘአመከርናሁ
በብዙኀ ወረከብናሁ ከመ ጸሐቂ ውእቱ በኵሉ፡ ወይ
እዜኒ ፈድፋደ ያስተፋጥን ይምጻእ ኀቤክሙ ወይጽ
ሕቅ በእንቲአክሙ እስመ ብዙኃ ያፈቅረክሙ ።
፳፫ ወእመኒ ቲቶ ሱታፌ ዘንኀብር ግብረ ምስሌሁ ወአኀ
ዊነ ሐዋርያት ዘቤተ ክርስቲያን ለስብሐተ እግዚአ
ሔር ።
፳፬ ወይእዜሰ አርእዩ ሎሙ ክሡተ ተፋቅሮተክሙ
ዝንቱ ውእቱ ዘበቱ ንትሜካሕ ብክሙ ንሕነ፡ ወይእ
ዜኒ አርእዩ በሙ በቅድመ ቤተ ክርስቲያን ።

ምዕራፍ ፱ ።

ክፍል ፲ወ፪፡ ዘከመ ይደሉ አስተዋጽኦ በፈቂድ ።

፩ ወበእንተሰ መልእክተ ቅዱሳን ብዙኀ ብየ ዘእጽሕፍ
ለክሙ ።
፪ እስመ አእመርኩ ከመ ትጽሕቁ አንትሙ ወበእን
ተዝ ንእድኩክሙ በኀበ ሰብአ መቄዶንያ ወእቤ
ሎሙ እስመ ሰብአ አካይያ አስተዳለዉ እምቀዳሚ
ዓም ወናሁ አጽሐቆሙ ተቃሕዎተ ዚአክሙ ለብዙ
ኃን ሰብእ ።
፫ ወፈነውናሆሙ ለአኀው ከመ ኢይኩነነ ሐሰተ በኀ
ቤሆሙ ዘንእድናክሙ በዝንቱ ወከመ ይርከቡክሙ
ድልዋኒክሙ በከመ ንቤሎሙ ።
፬ ወእመበ ከመ መጽኡ ምስሌየ ሰብአ መቄዶንያ ወረ
ከቡክሙ ዘእንበለ ታስተዳልዉ ንትኀፈር ንሕነኒ ወለ
ክሙኒ ከመ ኢይበሉክሙ አስተትክሙ ።
፭ አስተበቍዐክሙ አኀዊነ ግብረ ረስይዎ ወአስተዳ

የእናንተ ፍጹምነት የነዚያን ጕድለት ይመላልና፡ የነ ፲፬
ሱም ፍጹምነት የእናንተን ጕድለት ይመላልና፡ ኑሮ
አችሁ በሁሉ ትክክል ይሆን ዘንድ ። ምዕ ፱ ፲፪ ።
መጽሐፍ "ብዙ ያለው አላተረፈም ጥቂት ያለው አላ ፲፭
ጐደለም,, ብሏልና ። ዘፀ ፲፮ ፲፰ ።

ክፍል ፲፩ ፡ ለምእመናን ፍቅርን ስለ መግለጽ ።

ቲቶ እንደ ተናገረ ስለናንተ እንድናስብ ያደረገን እግ ፲፮
ዚአብሔር ይክበር ይመስገን ። ምዕ ፱ ፲፭ ።
ያመሰግናችኋልና ፍጹምነታችሁንም ወዷላችኋልና ፲፯
ጨክኖ ወደ እናንተ ሊመጣ ቸኵሏል ።
ስለ ትምህርቱ ምእመናን ሁሉ ያመሰገኑትን ወንድ ፲፰
ማችንንም ከእሱ ጋር ልከናል ። ምዕ ፲፪ ፲፰ ።
ወዲህም የቤተ ክርስቲያን ሹም ነው፡ ደስ ይለን ፲፱
ዘንድ እግዚአብሔርን ለማመስገን በምናገለግልበት
በዚች ጸጋም ከእኛ ጋር አንድ ነው ። ምዕ ፬ ፲፭ ።
መልእክታችሁንም እንዳታስነቅፉ ይህን ጠብቁ ። ፳
ኤፌ ፭ ፲፭ ።
ለሰውም ለእግዚአብሔርም መልካሙን ነገር አስቡ ። ፳፩
ምሳ ፫ ፬ ። ማቴ ፭ ፲፯ ።
ከነሱም ጋር በብዙ የፈተነውን በሁሉ ትጉህ ሁኖ ፳፪
ያገኘነውን ወንድማችንን ደግሞ አሁን ልከናል አሁ
ንም ወደ እናንተ ሊመጣ እጅግ ይፋጠናል ስለ እና
ንተም እጅግ ያስባል ይወዳችኋልና ።
በሥራ የምንተባበረው ቲቶም ቢሆን ወንድሞቻችን ፳፫
ሐዋርያትም ቢሆኑ ለእግዚአብሔር ክብር የቤተ ክር
ስቲያን ሹማምንት ናቸው ። ሮሜ ፲፮ ፯ ።
አሁንም ፍቅራችሁን በግልጥ አሳዩአቸው እኛ በእ ፳፬
ናንተ የምንመካበት ሥራ ይህ ነው ። አሁንም በም
እመናን ፊት ግለጡላቸው ። ምዕ ፯ ፲፬ ።

ምዕራፍ ፱ ።

ክፍል ፲፪፡ በፈቃድ ማዋጣት እንደሚገባ ።

ለቅዱሳን ስለሚደረገው አግልግሎት የምጽፍላችሁ ፩
ብዙ አለኝ ። ምዕ ፰ ፬ - ፭ ።
እናንተም እንደምትተጉ አውቃለሁና ስለዚህም ፪
የአካይያ ሰዎች ከዓምና ጀምሮ ገንዘብ አዘጋጅ
ተዋል ብዬ በመቄዶንያ ሰዎች ዘንድ አመሰግን
ኋችሁ ብዙዎችን ሰዎችን ከእናንተ ጋር መፈክ
ከር አትግቷቸዋልና ።
በዚህም ያመሰገንናችሁ ምስጋና በእነሱ ዘንድ ሐሰት ፫
እንዳይሆን እንደ ነገርናቸው ተዘጋጅታሁ ያገኟችሁ
ዘንድ ወንድሞቻችንን ላክን ። ምዕ ፰ ፳፬ ።
ምናልባት የመቄዶንያ ሰዎች ከእኔ ጋር የመጡ እን ፬
ደሆነ ገንዘቡን ሳታዘጋጁ ቢያገኙዋችሁ እኛም እናፍ
ራለን እናንተም ሥራት አፈረሳችሁ እንዳይሏችሁ ።
ወንድሞቻችን ፣ ይህን ግድ አድርጉት ብዬ እማልዳች ፭

| | |
|---|---|
| ልዉ ውእተ በረከተክሙ ወሥርዑ ዘነገርኩክሙ እንተ ላቲ ድልዋን አንትሙ፡ ወከመዝ ረስይዎ ከመ ዘበረከት ወአኮ ከመ ዘበ ትዕግልት ። | ኋለሁ ይህንንም በረከት የምታገኙበትን አዘጋጁ እና ንተ የተዘጋጃችሁላትን የነገርኳችሁን ፈጽሙ እንዲህ አድርጉት ተቀምቶ እንደሄደባችሁ ሳይሆን በረከት የምታገኙበት እንደመሆኑ አድርጉ ብዬ እነግራች ኋለሁ ። |
| ፮ ወዘሰ ጠዊዖ ይዘርእ ለዝንቱ ከማሁ ይጠውዖ ሎቱኒ ማእረሩ፡ ወዘሰ በበረከት ይዘርእ በበረከት የአርር ። | አሳንሶ የሚዘራ እንዲሁ መከሩ ያንስበታል፡ አብዝቶ የዘራ ግን በብዙ ያመርታል ። ምሳ ፲፩ ፳፬ ። ፲፱ ፲፯ ። መክ ፲፩ ፩-፮ ። ሉቃ ፮ ፴፰ ። ። ፮ |
| ፯ ወኵሉ በከመ አደሞ ልቡ ለይግበር እስመ ኢኮነ በአገብሮ ዳእሙ በፍሥሐ ለየሀቡ፡ እስመ ከማሁ ያፈቅር እግዚአብሔር ። | ሁሉ ልቡ እንደወደደ ያድርግ ደስ ብሏቸው ይስጡ እንጂ በግድ አይደለምና እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ስጦታ ይወዳልና ። ዘፀ ፳፭ ፪ ። ዘዳግ ፲፭ ፯ ። ፯ |
| ፰ ወይክል እግዚአብሔር አፈድፍዶ ለክሙ ኵሎ በረከቶ ያብዝኅ ለዝሉፉ ወታተርፍዎ ለኵሉ ወታፈድፍዱ በኵሉ በምግባረ ሠናይ ። | እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ፍጹም በረከቱን ሊያበዛላችሁ ይችላል እናንተም በፍጹም ምግባር አብዝታችሁ ለሁሉ ታተርፉታላችሁ ። መዝ ፹፱ ፲፩ ። ፰ |
| ፱ በከመ ይቤ መጽሐፍ ዘረወ ወወሀበ ለነዳይ፡ ወጽድቁኒ ይነብር ለዓለም ። | መጽሐፍ "በተነ ለድኻ ሰጠ፡ ጽድቁም ለዘለዓለም ይኖራል„ ብሎ እንደ ተናገረ ። መዝ ፻፲፪ ፱ ። ፱ |
| ፲ ወውእቱ ይሁብ ዘርአ ለዘራኢ ወእክለ ለሲሳይ ያሠምር ወያበዝኅ ለክሙ ማእረረ ጽድቅክሙ ። | እርሱ ዘርን ለዘሪ እህልንም ለተመጋቢ ይሰጣል የጽድቃችሁንም አዝመራ ያሠምርላችኋል ያበዛላችኋል ። ዘፍ ፩ ፲፩-፲፪ ። ኢሳ ፶፭ ፲ ። ሆሴዕ ፲ ፲፪ ። ፲ |
| ፲፩ ከመ ትብዐሉ በኵሉ ትፍሥሕት እንተ ትገብር ለክሙ አኰቴተ እግዚአብሔር በእንተ ብዙኃን ። | ሰብዙ ሰዎች ስለ ሰጣችሁ የእግዚአብሔርን ምስጋና በምታደርግላችሁ በፍጹም ደስታ ትክብሩ ዘንድ ። ፲፩ |
| ፲፪ እስመ ዛቲ መልእክተ ዝንቱ ግብር አኮ ለዝንቱ በሕቲቱ ዘታሠልጥ እስመ ትፌጽም ሎሙ ተፅናሰሙ ለቅዱሳን ዓዲ ወታፈደፍድ አኰቴተ እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳን ። | ስለዚህ ሥራ የምትደረገው ይህቺን አገልግሎት ግዳጅ የምትፈጽም ለዚህ ብቻ አይደለም የቅዱሳንን ችግር ታሟላለችና በቅዱሳንም ዘንድ የእግዚአብሔርን ምስጋና ታበዛለችና ። ምዕ ፰ ፲፬ ። ፲፪ |
| ፲፫ ወየአኵትዎ ለእግዚአብሔር በመከራሃ ለዛቲ ሃይማኖትክሙ እስመ ተአመንክሙ ለመልእክተ ክርስቶስ ወኀበርክሙ ተፈሢሐክሙ ወአስተዋፃእክሙ ኵልክሙ ። | በዚች በሃይማኖታችሁ ፈተና ምክንያት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ክርስቶስ ላስተማራት ትምህርት ታዝዛችኋልና ሁላችሁም ደስ ብሏችሁ ተባብራችሁ አወጣጥታችኋልና ። ፲፫ |
| ፲፬ ወእሙንቱኒ ይጼልዩ በእንቲአክሙ ወይፈትዉ ይርአዩክሙ በእንተ ጸጋ እግዚአብሔር ዘላዕሌክሙ ። | እነሱም ስለ እናንተ ይጸልያሉ ስለ አደረችባችሁ የእግዚአብሔር ጸጋም ሊያዩአችሁ ይመኛሉ ። ማቴ ፰ ፲፮ ። ዕብ ፲፫ ፲፮ ። ፲፬ |
| ፲፭ አኰቴት እግዚአብሔር በእንተ ጸጋሁ ኢትተረጐም ወትመጽእ እመ ኢትሐዘብዋ ። | ስለማትመረመር ባላሰቧትም ጊዜ ስለምትመጣ ጸጋው፡ እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው ። ያዕ ፩ ፲፯ ። ፲፭ |

| ምዕራፍ ፲ ። | ምዕራፍ ፲ ። |
|---|---|
| ክፍል ፲ወ፫፡ በእንተ ኃይለ እግዚአብሔር ። | ክፍል ፲፫፡ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ። |
| ፩ አስተበቍዐክሙ አነዊ አነ ጳውሎስ በየውሃት ወበ ምሕረተ ክርስቶስ እስመ ሰበ እሄሉ ኀቤክሙ መጠነ በገጽ ወበኀበሰ ኢሀሎኩ እትኄፈ ላዕሌክሙ ብቍዑኒ እስመ እንዘ ኢሀሎኩ ትትአመን በአፍቅሮትክሙ ። | ወንድሞቻችን፤ እኔ ጳውሎስ በክርስቶስ ቸርነትና በደግነቱ እማልዳችኋለሁ ከእናንተ ዘንድ በነበርኩ ጊዜ ከፊታችሁ የመኖሬን ያህል በቃል እነግራችኋለሁ፡በሌለሁበት ጊዜ ግን እጽፍላችኋለሁ በጄ በሉኝ፡ ሳልኖርም እንደምትወዱኝ አምናለሁና ። ፪ ቆሮ ፪-፫ ። ፩ |
| ፪ ከመ ኢይሥራሕ እመ መጻእኩ ኀቤክሙ ወእትኀበል አጥብዕ እስመ ብ እለ ይትሔዘቡነ ከመ በሕገ ሥጋ ነሐውር ። | ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ እንዳልደክም በሥጋዊ ሥራት እንደምንኖር አድርገው የሚጠረጥሩን አሉና ጨክኜ እሠራለሁ ። ቍ ፲፩ ። ፪ |
| ፫ በሥጋነሰ ነሐውር ወአኮ በሕገ ዚአሁ ዘነሐውር ወዘ ንፀብእ ። | በሥጋችንስ እንኖራለን፡ ግን በእሱ ሕግ የምንኖር የምንዋጋ አይደለም ። ፫ |

፬ እስመ ንዋየ ሐቅሉ ለፀብእነ ኢኮነ በሕገ ሥጋ አላ በኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ ዘይነሥት አጽዋናተ ፅኑዓነ ።

የሰልፋችን መሣሪያ ፅኑ ፅኑ ምሽጎችን በሚያፈርስ በእግዚአብሔር ኃይል ነው እንጂ በሥጋ ሥርዓት አይደለምና ። ኤር ፩ ፲ ። ኤፌ ፮ ፲፫ - ፲፯ ። ፬

፭ ወያነህል ኵሎ ዘይትዔበይ ወይትሌዓል ላዕለ ክርስቶስ ከመ ይጊወዉ ኵሉ ልብ ወሕሊና ይግነይ ለእግዚአብሔር ።

በክርስቶስ ላይ የሚታበየውንና ከፍ ከፍ የሚለውን ሁሉ በሚያጠፋ ልብ ሁሉ ያምን ዘንድ ሕሊናም ሁሉ ለእግዚአብሔር ይገዛ ዘንድ ። ፭

፮ ወድልዋን ንሕነ ንትበቀሎ ለዘኢይገርር ወኢይሰምዕ ሶአመ ፈጸምክሙ አንትሙ ትእዛዘ ዘመንገለ ገጽ ርእዩ ዘቅድሜክሙ ።

ሰምቶ የማይታዘዘውን ልንበቀለው ዝግጁዎች ነን ወደፊት እንድትሄዱ የሚያደርጋችሁን ትእዛዝ በፈጸማችሁ ጊዜ ወደ ፊታችሁ ተመልከቱ ። ኤር ፳ ፬ ። ፮

፯ ወዘሂ ተአመነ በክርስቶስ ከመዝ ለየሐሊ ለሊሁ እስመ በከመ ክርስቶስ ከማሁ ንሕነሂ ።

በክርስቶስ ያመነ ሰው እርሱ እንዲህ ያስብ ፡ እኛም እንደዚሁ እንደ ክርስቶስ ነንና ። ምዕ ፲፩ ፳፫ ። ፯

፰ ወእመኒበ ዘተመከሕኩ ፈቂድየ በሢመትክሙ እንተ ወሀበኒ እግዚአብሔር ለተሐንፆትክሙ ወአኮ ለተነሥቶ ኢይትኀፈር ።

ለማፍረስ ያይደለ እናንተን ለማነፅ እግዚአብሔር ለሰጠኝ ሹመት የተመካሁት ትምክሕት ቢኖር አላፍርም ። ምዕ ፲፪ ፮ ። ፩ ቆሮ ፭ ፪ ። ፬ ፭ ። ፰

፱ ወበሕቱ እምህክ ዘንተ ከመ ኢይምሰሎ ለዘይትሐዘብ ከመ ዘአጌርመክሙ በመጻሕፍትየ ።

ግን ለሚጠራጠር ሰው በመጻሕፍቶቼ የማስፈራራ እንዳይመስለው ይህን እተወዋለሁ ። ፱

፲ እስመበ እምሰብእ ዘይብል እስመ መጻሕፍቲሁሰ ክቡዳት ወዕፁባት ወሀልዎቱሰ በሥጋ ድኩም ውእቱ ወነገሩሂ ሕፁር ።

ከሰዎች መካከል መጻሕፍቶቹ ከባዶች አስጨናቂዎች ናቸው በሥጋ አኗኗሩ ግን ደካማ ነው ፡ ነገሩም ትርታ ነው የሚል አለና ። ገላ ፬ ፲፫ ። ቀኍ ፩ ። ፲

፲፩ ወበሕቱ ዘንተ ነገረ ያእምር ዘይቄል ዘንተ ከመ በቃልነ በውስተ መጻሕፍት አመ ኢሀለውነ ከማሁ በምግባርነሂ አመ ሀለውነ ።

ነገር ግን ይህን የሚል በሌለንበት ጊዜ በመጻሕፍት እንደሚገለጠው እንደ አነጋገራችን ባለን ጊዜም በሥራችን እንዲሁ እንደሆነ ይህን ነገር ይወቅ ። ፲፩

፲፪ ወኢንትሃበል ናጥብዕ ነሐሊ ሰርእሰነ ለሊነ ከመ እለ ይንእዱ ርእሰሙ በዘእመከሩ ወአየኑ ለሊሆሙ ወኢየአምሩ ፍካሬሁ ዘለሊሆሙ ይነብቡ ።

ራሳቸው በአሰቡት በግመገሙት መጠን ራሳቸውን እንደሚያመሰግኑ ራሳቸውም የሚናገሩትን ትርጓሜውን እንደማያውቁ ሰዎች አድርገን ለራሳችን ልና ስብ ፈጽሞ አንሞክርም ። ምዕ ፫ ፩ ። ፭ ፲፪ ። ፲፪

፲፫ ወንሕነሰ ኢንትመከሕ ፈድፋደ እምዐቅምነ ዘእንበለ በመስፈርት ወሕግ ዘአቀመ ለነ እግዚአብሔር እስከ ንበጽሕ ኀቤክሙ ።

እኛስ ወደ እናንተ እስክንደርስ ድረስ እግዚአብሔር በወሰነልን ሕግና ሥርዓት እንጂ ከዓቅማችን አልፈን አንመካም ። ሮሜ ፲፪ ፫ ። ፲፫

፲፬ እስመ አኮ ዘንዌድስ ርእሰነ ከመ ዘኢበጻሕነ ኀቤክሙ ዳእሙ በጸሕነ ኀቤክሙ ውስተ ትምህርተ ክርስቶስ ።

ወደ እናንተ እንዳልደረስን አድርገን ራሳችንን የምናመሰግን አይደለምና ፡ የክርስቶስን ሕግ በማስተማር ወደ እናንተ ደርሰናል እንጂ ። ፩ ቆሮ ፱ ፩ ። ፲፬

፲፭ ወንሕነሰ ኢንትሜከሕ በዘኢይረትዕ በፃማ ነኪር ወበሕቱ ንሴፎ ትብዛኀ ሃይማኖትክሙ ወትዕበይ በላዕሌክሙ ሕገ ሥርዓትክሙ ።

እኛስ በማይገባው ሌላ በደከመበት አንመካም ፡ ነገር ግን ሃይማኖታችሁ እንድትሰፋ የተሠራችላችሁ ሕግም በእናንተ ላይ እንድትፀና ተስፋ እናደርጋለን ። ሮሜ ፲፭ ፳ ። ፲፭

፲፮ ወፈድፋደ ንሜህረክሙ ወእሜሃ የዐቢ ምስሌሁ እምጣንነ ወንሕነሰ ኢንትሜከሕ በዘኢይረትዕ ወበዘኢይደሉ ።

ሕብዝተንም እናስተምራችኋለን ያን ጊዜ መጠናችን ከሥራችን ጋር ከፍ ከፍ ይላል እኛስ በማይቀናና በማይገባ እንመካም ። ፲፮

፲፯ ወዘሰ ይትሜከሕ በእግዚአብሔር ለይትመከሕ ።

የሚመካ ግን በእግዚአብሔር ይመካ ። ኤር ፱ ፳፫ - ፳፬ ። ፩ ቆሮ ፩ ፴፩ ። ፲፯

፲፰ ወአኮ ዳእሙ ዘርእሶ ንእደ ኅሩየ ይከውን ፡ አኮኑ ዘእግዚአብሔር ንእዶ ከመ ።

ራሱን ያከበረ ብቻ የሚከብር አይደለም ፡ እግዚአብሔር ያከበረው ይከብራል እንጂ ። ሉቃ ፲፰ ፲፬ ። ፲፰

ምዕራፍ ፲ወ፩ ።

ክፍል ፲ወ፬ ፡ በእንተ ኢ.ተወክፎ ትምህርተ ባዕድ።

፩ ወርቱዕሰ ትትዐገሡኒ ኅዳጠ ከመ እንብብ በዕበድየ እንዘ ትትዔገሡኒ ።
፪ እስመ እቀንእ ለክሙ ቅንአተ እግዚአብሔር እስመ ፈኀርኩክሙ ለአሐዱ ምት ድንግል ወንጹሕ ክርስ ቶስ ከመ አቅርብክሙ ኀቤሁ ።
፫ ወባሕቱ እፈርህ ዮጊ ከመ አርዌ ምድር አስሐታ ለሔዋን በጕኅሉት እንዳዒ ለእመ ይማስን ልብክሙ እምየውሀቱ ወንጽሑ ለክርስቶስ ።
፬ ሰበሁ ከነ ዘይመጽእ ኀቤክሙ ዘጸውዐክሙ ኀበ ካልእ ዘኢ.ሰበክነ ለክሙ ፡ ወእመበ ካልእ መንፈስ ዘትነሥኡ ዘኢ.ነሣእክሙ ፡ ወእመኒበ ካልእ ትምህርት ዘኢ.ተመሀርክሙ ርቱዕ ትጽንሑነ ።
፭ ወባሕቱ እትሔዘብ አልቦ ዘአሕፀፅኩክሙ ዘእምበ ፅዓን ሐዋርያት ።
፮ ወእመኒ ዐብድ አነ በቃልየ አኮኬ በልብየ ወባሕቱ እክሥት ለክሙ ኵሎ ውስተ ኵሉ ።
፯ ወሚመ አበስኩኑ እንጋ ዘአሕመምኩ ርእስየ በኵሉ ከመ አንትሙ ትትለዐሉ እስመ በከንቱ መሀርኩ ክሙ ትምህርተ እግዚአብሔር ።
፰ ወባዕደሰ ቤተ ክርስቲያን ቀሠጥኩ ወነሣእኩ ለሲሳ ይየ ከመ እትለአክሙ ወአመሂ ሀለውኩ ኀቤክሙ ኢ.ተሰቆቁ ንዋየክሙ እንዘ እጼነስ ።
፱ ወኀበሂ ኢ.ያእከልኩ ሥለጡ ሊ.ተ አኀዊነ በጺ.ሐሙ እመቄዶንያ ወበኵሉ ተዐቀብኩ ከመ ኢ.ያክብድ ላዕ ሌክሙ ወእትዐቀብኒ ።
፲ እስመ ጽድቁ ለክርስቶስ ይሄሉ ምስሌየ ወኢ.ተዐፅ ወተኒ ዘቲ ፍሥሐየ በደወለ አካይያ ።
፲፩ በእንተ ምንት እስመሁ እንጋ ኢ.ያፈቅረክሙኑ እን ከሰ እግዚአብሔር የአምር ዘንተ ።
፲፪ ወባሕቱ ዘኒ ገበርኩ ወዘኒ እገብር ከመ እክልአሙ ምክንያተ ለእለ ይፈቅዱ ምክንያተ ከመ ኢ.ይርከቡ እሙንቱኒ በዘይትሜክሑ ከማነ ።
፲፫ እስመ ሀለዉ. ሐሳውያን ገበርተ ዐመፃ እለ ይትሚ የኑ ወይትሜሰሉ ሐዋርያተ ክርስቶስ ።
፲፬ ወዝኒ አኮ ለአንክሮ እስመ ለሊ.ሁ ሰይጣን ይትሜሰል ከመ መልአከ ብርሃን ።
፲፭ ወዘኒ ኢ.ኮነ ዐቢየ ለእመ ይትሜሰሉ መላእክቲሁኒ ከመ መላእክተ ጽድቅ ወደኃሪቶሙሰ በከመ ምግ ባሮሙ ።

ክፍል ፲ወ፭ ፡ በእንተ ዘኢ.ርቱዕ ተመክሖ ።

፲፮ ወካዕበ እብል አልበ ዘይሬስየኒ ከመ ዐብድ ወእመአ ኮሰ ከመ ዐብድኒ ተወከፉኒ ከመ እትመካሕ አነሂ ኅዳጠ ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

ክፍል ፲፬ ፡ የባዕዳንን ትምህርት ስለ አለመቀበል ።

አገባብስ ጥቂት ልትታገሡኝ ይገባል ፡ ታግሣችሁኝ ፩
በስንፍናየ እናገር ዘንድ ። ምዕ ፭ ፲፫ ።
ለእግዚአብሔር የሚገባ ቅናት እቀናላችኋለሁ ወደ ፪
ርሱ አቀርባችሁ ዘንድ ለአንድ ንጹሕ ድንግል
ሙሽራ ለኢየሱስ ክርስቶስ አጭቻችኋለሁና ።
ነገር ግን ምናልባት የምድር እባብ ሔዋንን በተን ፫
ኰል እንዳሳታት እንጂ ልቡናችሁ ከክርስቶስ ከደ
ግነቱ ከንጽሕናው ወጥቶ ይለወጥ እንደሆነ ብዬ እፈ
ራለሁ ። ዘፍ ፫ ፬ - ፲፫ ።
ወደናንት የሚመጣ እኛ ወደ አላስተማርናችሁ ወደ ፬
ሌላ ኢየሱስ የጠራችሁ ቢኖር ፡ ያል ተቀበላችሁ የም
ትቀበሉት ሌላ መንፈስ ቢኖርም ያልተማራችሁት
ሌላ ትምህርት ቢኖርም እንኳ ልትጠብቁን ይገባል ።
ነገር ግን ከሌሎች ሐዋርያት ያጐደልኩበችሁ የሌለ ፭
ይመስለኛል ። ምዕ ፲፪ ፲፩ ። ፩ ቆሮ ፲፭ ፲ ።
እኔ በነጋገሬም አላዋቂ ብሆንም በልቤ አይደለም ፡ ፮
ግን ሁሉን በሁሉ እገልጥላችኋለሁ። ፩ ቆሮ ፪ ፩ ።
ወይስ እናንተ ከፍ ከፍ ትሉ ዘንድ በከንቱ የእግዚ ፯
አብሔርን ትምህርት ስለ አስተማርኳችሁ በሁሉ
ራሴን ያዋረድኩ በደልኩን ? ። ፩ ቆሮ ፱ ፲፪ - ፲፰ ።
ግን ከሌሎች ምእመናን እናንተን አገለግል ዘንድ ፰
ለምግቤ ያህል ተቀበልኩ ፡ ከእናንተ ዘንድ በነበር
ኩበት ጊዜም ስቸገር ለገንዘባችሁ አልሳሳሁም ።
ባልበቃኝም ጊዜ ወንድሞቻችን ከመቄዶንያ መጥ ፱
ተው አሟሉልኝ እናንተን እንዳላስቸግራችሁ በሁሉ
ተጠነቀቅሁ ወደፊትም እጠነቀቃለሁ ። ምዕ ፲፪ ፲፫ ።
የክርስቶስ ጽድቁ አብሮኝ ይኖራልና ይህቺም ጸጋዬ ፲
በአካይያ አውራጃ አልተቋረጠችብኝም ።
ስለ ምን ነው ? አልወዳችሁምና ነውን ? እንጂ ፲፩
እንኪያስ እንደምወዳችሁ እግዚአብሔር ያውቃል ።
ግን ያደረግሁትም የማደርገውም ቢሆን ምክንያት ፲፪
ለሚሹት ሰዎች ምክንያትን አሳጣቸው ዘንድ ነው ፡
እነሱም እንደኛ የሚመኩበትን እንዳያገኙ ።
የሚተናኰሉ የክርስቶስ ሐዋርያት ነን የሚሉ ዐመ ፲፫
ፅን የሚያደርጉ ሐሰተኞች አሉና ። ምዕ ፪ ፲፯ ።
ይህም አያስደንቅም እሱ ራሱ ሰይጣን የብርሃን መል ፲፬
አክ መስሎ ይመጣልና ።
ይህም ታላቅ ነገር አይደለም የሰይጣን መልእክተ ፲፭
ኞች የእውነት መላእክትን ቢመስሉ ፍጻሜውያ
ቸው ግን እንደ ሥራቸው ነው ።

ክፍል ፲፭ ፡ መመካት ስለማይገባ ።

ደግሞም እንዲህ እላለሁ ፡ እንደ ሰነፍ የሚቈጥረኝ ፲፮
አይኑር ያለዚያስ እንደ ሰነፍ እንኳ ብሆን ተቀበሉኝ
እኔም ጥቂት እመካ ዘንድ ። ምዕ ፲፪ ፮ ።

፲፯ ወዝኒ አኮ ዘመንገለ እግዚአብሔር ዘእነግር ዳእሙ
ከመ ዐብድ እዘነግዕ በእንተ ዛቲ ትምክሕትየ ።

፲፰ እስመ ብዙኃን እለ ይትሜክሑ በሕግ ዘሥጋ አነሂ
እትሜካሕ ።
፲፱ ወእመሰ ይኤድመክሙ አዕምአቶሙ ለዐብዳን እንዘ
ጠቢባን ወነበብያን አንትሙ።
፳ እስመ ትትዔገሥዎሙ ለእለ ይትዔገሉክሙ ወለእ
ለሂ የኀይዱክሙ ለእለሂ ይበልዑክሙ ወለእለሂ
ይትዔበዩ ላዕሌክሙ ወለዘሂ ይጸፍዕክሙ ገጸክሙ ።
፳፩ እብል ዘንተ ከመ ዘያስተሐቅር ከመ ሕሙማኒሁ
ንሕነ ለክሙ እብል አነሂ በዕበድየ አልቦ ዘይትሐ
በል ላዕሌየ ዘእብል ዳእሙ ዘአነ እትሐበል ላዕሌሁ ።

፳፪ እመኒ ዕብራውያን እሙንቱ አነሂ ከማሆሙ ፤ ወእመኒ
እስራኤላውያን እሙንቱ አነሂ ከማሆሙ ፤ ወእመኒ
ዘርአ አብርሃም እሙንቱ አነሂ ከማሆሙ ።

፳፫ እመኒ ላእኩ ለክርስቶስ እሙንቱ አኮሁ እዘነግዕ
ለርእስየ በፃማሂ አፈድፈድኩ ፤ ወበተቀሥፎሂ አፈድ
ፈድኩ ፤ ወበተሞቅሖሂ አብዛኅኩ ፤ ወለሞትኒ ብዙኃ
ተደለውኩ ።
፳፬ ኃምሰ ቀሠፉኒ አይሁድ በበአርባዓ ዘእንበለ አሐቲ ።
፳፭ ሥልሰ ዘበጡኒ በአብትር ፤ ምዕረ ወገሩኒ በአእባን ፤
ሥልሰ ሰኰየት ሐመርየ ፤ ቤትኩ ወወዐልኩ እንዘ
እጸብት ውስተ ዕመቀ ባሕር ።

፳፮ ወበመንገድሂ ዘልፈ እትመነደብ በተከዚኒ እመንደ
ቡኒ ፈያት ፤ እመንደቡኒ አዝማድየ ፤ እመንደቡኒ አሕ
ዛብ ፤ ተመንደብኩ በሀገር ፤ ወተመንደብኩ በሐቅል
ተመንደብኩ በባሕር ፤ አመንደቡኒ ቢጽ ሐሳውያን ።

፳፯ በፃማ ወበሥራሕ ፤ ወበትጋሀ ብዙኀ ፤ በረኃብ ወበጽ
ምዕ ፤ በጾም ብዙኀ ወበቍር ወበዕርቃን ።

፳፰ ወዘእንበለዝ ብዙኀ በዕድ ዘረከበኒ ኵሉ አሚረ እንዘ
እሔሊ ቤተ ክርስቲያናት ።
፳፱ መኑ ዘይደዊ ወኢየሐምም አነ ፤ ወመኑ ዘይስሕት
ወኢይደነግፅ ።
፴ ወእመሰ ይደሉ ተመክሖ ፤ አነኒ እትሜካሕ በሕማ
ምየ ።
፴፩ የአምር እግዚአብሔር አቡሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ
ክርስቶስ ዘውእቱ አምላክ ቡሩክ ፤ ለዓለመ ዓለም
ከመ ኢይሔሱ ።
፴፪ በሀገረ ደማስቆ መልአከ አሕዛብ ዘእምታሕተ አርስ
ጣስዮስ ንጉሥ ዐቃቤ ሀገር ደማስቆናዊ ፈቀደ የአ
ኅዝኒ ።



ይህም የምናገረው በእግዚአብሔር ዘንድ የሚገባ ፲፯
አይደለም ፤ ስለዚህች መመከቴ እንደ ሰነፍ መምሰሌ
ነው እንጂ ። ምዕ ፱ ፬ ።
በሥጋዊ ሥርዓት የሚመኩ ብዙዎች ናቸውና እኔም ፲፰
እመካለሁ ። ኤር ፱ ፳፫ - ፳፬ ። ፊል ፫ ፫ ።
እናንተ ባለ አእምሮ ዐዋቂዎች ስትሆኑ ሰነፎቹን ፲፱
መስማት ደስ የሚያሰኛችሁ ከሆነ ።
የሚታገሏችሁን የሚቀሟችሁን የሚበድሏችሁን ፳
የሚታበዩባችሁን ፊታችሁን የሚመታችሁን ትታገ
ሏቸዋላችሁና ። ገላ ፪ ፬ ።
ይህን ንቆ እንደሚያቃልል ሰው እናገራለሁ እኛ ለና ፳፩
ንተ በሽተኞች መሆናችን ነውን ? እኔም ብሠለጥን
በት እንጂ የሚሠለጥንብኝ የለም እላለሁ ። ፩ ቆሮ
፩ ፲፯ ። ገላ ፬ ፲፫ ።
እነሱ ዕብራውያን ቢሆኑ እኔም እንደነሱ ዕብራዊ ፳፪
ነኝ ፤ እነሱ እስራኤላውያንም ቢሆኑ እኔም እንደነሱ
እስራኤላዊ ነኝ ፤ እነሱ የአብርሃም ልጆች ቢሆኑ
እኔም እንደነሱ ነኝ ፊል ። ፫ ፭ ።
እነሱ የክርስቶስ አገልጋዮች ነን ቢሉ ለራሴ እዘነጋ ፳፫
የለምን ? በድካም ብዙ ደክሜያለሁ ፤ በመገረፍ ብዙ
ደክሜያለሁ ፤ በእሥራትም ብዙ ጊዜ ታሥሬአለሁ ፤
ለሞት ብዙ ጊዜ ተዘጋጅቼአለሁ ። ፩ ቆሮ ፲፭ ፪ ።
አንዲት ሳትቀር አምስት ጊዜ አርባ አርባ ገረፉኝ ። ፳፬
ሦስት ጊዜ በበትር ደበደቡኝ ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ፳፭
ዮች ወገሩኝ ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተንከራተተች ፤
በጥልቁ ባሕር ስዋኝ አድሬ ስዋኝ ዋልኩ ። ግ. ሐ.
፲፬ ፲፱ ። ፲፮ ፳፪ ።
በጕዞም ዘወትር መከራ እቀበል ነበር በፈሳሽ ወኃም ፳፮
ወንበዶች አሠቃዩኝ ፤ ዘመዶቼም አስጨነቁኝ ፤ አሕዛ
ብም መከራ አፀኑብኝ ፤ በከተማ መከራ ተቀበልኩ ፤
በዱርም በባሕርም መከራ ተቀበልኩ ፤ ክርስቲያን
ነን ባዮችም መከራ አፀኑብኝ ።
በመውጣት በመውረድ ፤ በድካም በብዙ ትጋት ፳፯
በመራብ ፤ በመጠማት አብዝቶ በመጾም ፤ በመራቈት
በብርድ በዚህ ሁሉ መከራ ተቀበልኩ ። ምዕ ፮ ፩ ።
ከዚህም በቀር ለቤተ ክርስቲያን ሳስብ ዘወትር ያገ ፳፰
ኘኝ ልዩ ልዩ መከራ ብዙ ነው ። ግብ ሐዋ ፳ ፲፰ ።
ታሞ እኔ የማላዝንለት ማነው ? በድሎስ እኔ የማል ፳፱
ደነግጥለት ማነው ? ። ፩ ቆሮ ፱ ፳፪ ።
መመካት የሚገባስ ከሆነ እኔም በመከራዩ እመካለሁ ። ፴

ሐሰት እንዳልናገር ለዘለዓለም የባሕርይ አምላክ ፴፩
የሚሆን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባቱ እግዚ
አብሔር ያውቃል ። ምዕ ፩ ፳፫ ።
በደማስቆ ከተማ ከአርስጣስዮስ ንጉሥ በታች ፴፪
የሚያዘው የሕዝብ ሹም አገር አሳዳሪ የነበረው የደ
ማስቆ ሰው ሊይዘኝ ወደደ ።

፴፫ ወአውረዱኒ በሰብሳብ እንተ መስኮት እምዓረፍት
ወአምሰጥኩ እምእዴሆሙ ።

ምዕራፍ ፲ወ፪ ።

**ክፍል ፲ወ፩ ፤ በእንተ ዘከመ ኢይደሉ ተመክሖ ።**

፩ ወናሁ ይረትዕ ሊተ ተመክሖ ወባሕቱ ኢኮነ ሠናየ ፤
ንግባእ ካዕበ ወንዘክር ራእየ ዘከሠተ እግዚአብሔር ።

፪ አአምር ብእሴ ምእመነ በክርስቶስ እምቅድመ ዐሠ
ርቱ ወአርባዕቱ ዓመት እመኒ በሥጋሁ ወእመኒ ዘእ
ንበለ ሥጋሁ እንዳዒ እግዚአብሔር የአምር ወመሰ
ጥዎ ለውእቱ ብእሲ እስከ ሣልስ ሰማይ ።

፫ ወአአምሮ ለውእቱ ብእሲ እመኒ በሥጋሁ ወእመኒ
ዘእንበለ ሥጋሁ እንዳዒ እግዚአብሔር የአምር ።
፬ ወመሰጥዎ ውስተ ገነት ወሰምዐ ህየ ነገረ ዘኢይተ
ረጎም ዘኢይከውኖ ለእጓለ እመሕያው ይንብብ ።
፭ ወበእንተ ዝንቱኬ በዘከመዝ እትሜካሕ በርእስየ
ኢይትሜካሕ ዘእንበለ በሕማምየ ።
፮ ወእመኒ ፈቀድኩ እትመካሕ ኢኮንኩ ዓብደ እስመ
ጽድቀ እነግር ፤ ወባሕቱ እምሕከ ከመ ኢይትሐዘቡኒ
በዘርእዩኒ ወበዘሰምዑኒ ፈድፋደ ።
፯ ወበእንተዝ ከመሰ ኢይትዐበይ በብዙኅ ራእይ ተው
ህበኒ መልአከ ሰይጣን ዘይደጐፅኒ ሥጋየ ወይኰርዓኒ
ርእስየ ።
፰ ወአስተብቋዕክዎ ለእግዚእየ ሥልሰ በእንቲአሁ ከመ
ያእትቶ እምኔየ ።
፱ ወይቤለኒ የአክለከ ጸጋየ ወኃይልሰ በደዌ የሐልቅ
ወሠመርኩ እትመካሕ በሕማምየ ከመ ይኅድር
ኃይለ ክርስቶስ ላዕሌየ ።
፲ ወበእንተ ዝንቱ ሠመርኩ በሕማምየ በተጽዕሎሂ
ወበምንዳቤሂ ወበተሰዶሂ ወበተጽናስሂ በእንተ ክር
ስቶስ እስመ ሶበ አሐምም ሶቤሃ እፀንዕ ።

፲፩ ወናሁ ኮንኩ ዓብደ በተመክሖትየ በዘአንትሙ አገ
በርክሙኒ ወሊተሰ ርቱዕ እክበር በኀቤክሙ ወትኩ
ኑኒ ሰማዕትየ እስመ ዘአሐፀፅኩክሙ እምዘኵሉ
ሐዋርያት ወእመኒ ከመ ወኢምንት አነ ።

፲፪ ትምህርተ ሐዋርያትሰ ተገብረ ለክሙ በኵሉ ትዕግ
ሥት ወበተአምራት ወመንክራት ወኃይላት ።

፲፫ ወምንተኑ ዘአሐፀፅኩክሙ ወዘአኅጣእኩክሙ እም
ኵሉ ቤተ ክርስቲያናት ዘእንበለ ዛቲ እንተ ኢመጻ
እኩ ኀቤክሙ አሥርሕክሙ ጻግዉንያ ለዛቲ አበሳየ።
፲፬ ናሁ ሣልስየ ዝንቱ እንዘ አስተዳሉ እምጻእ ኀቤ
ክሙ ወኢተፋጠንኒ እስመ ኢያክሙ እፈቅድ ወአኮ

በቅርጫት አድርገው በመስኮቱ በኩል ከአጥሩ ላይ ፴፫
አወረዱኝና ከእጁ አመለጥኩ ግብ ሐ ፱ ፳፬-፳፭ ።

ምዕራፍ ፲፪ ።

**ክፍል ፲፩ ፤ መመካት ስለ ማይገባ ።**

እነሆ መመካት ይገባኛል ግን የሚገባ አይደለም ዳግ ፩
መኛም መለስ ብለን እግዚአብሔር የገለጠውን
ራእይ እናስታውስ ።
ከዐሥራ አራት ዓመት በፊት በክርስቶስ ያመነ አንድ ፪
ሰው ዐውቃለሁ በሥጋውም እንደሆነ ያለ ሥጋ
ውም እንደሆነ እንጃ እግዚአብሔር ያውቃል ፤ ያንን
ሰው እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ነጥቀው ወሰ
ዱት ።
ያንን ሰው ዓውቀዋለሁ በሥጋው እንደሆነ ያለ ፫
ሥጋውም እንደሆነ እንጃ እግዚአብሔር ያውቃል ።
ወደ ገነትም ነጥቀው ወሰዱት በዚያም የማይተረ ፬
ጐም የሰው ልጅ ሊናገረው የማይቻለውን ነገር ሰማ።
ስለዚህ በእንደዚህ ያለው ነገር እመካለሁ በመከራዬ ፭
እንጂ በራሴ አልመካም ። ምዕ ፲፩ ፴ ።
ልመካም ብወድ አላዋቂ አይደለሁም እውነቱን እና ፮
ገራለሁና ፤ ግን በዩኝ በሰሙኝ እጅግ እንዳይጠራጠ
ሩኝ ገምግሜ እተዋለሁ ። ምዕ ፲ ፰ ። ፲፩ ፲፮ ።
ስለዚህም ቢሆን በብዙ ራእይ እንዳልታበይ ሰውነ ፯
ቴን የሚወጋኝ ራሴን የሚቀጠቅጠኝ የሰይጣን መል
እክተኛ ተሰጠኝ ። ኢዮ ፪ ፯ ።
ከእኔ ያርቀው ዘንድ ስለ እርሱ ጌታዬን ሦስት ጊዜ ፰
ማለድኩት ። ዘዳግ ፫ ፳፫ ። ማቴ ፳፮ ፴፱ ።
ጸጋዬ ይበቃኻል ኃይልስ በደዌ ያልቃል የክርስ ፱
ቶስ ኃይሉ በእኔ ላይ ያድር ዘንድ በመከራዬ ደስ
ይለኛል ። መክ፡ ፯ ፲፰ ። ኢሳ፡ ፵ ፳፱ ።
ስለዚህም መከራዬ ልቀበል ወደድኩ በመሰደብም ፲
ቢሆን በመጨነቅም ቢሆን በመሰደብም ቢሆን ስለ
ክርስቶስ በመቸገርም ቢሆን መከራ በተቀበልኩ
ጊዜ ወዲያው እፀናለሁና ። ፊልጵ ፬ ፲፫ ።
እናንተ ስላገበራችሁኝ በመመካቴ እነሆ ሰነፍ ሆንኩ ፲፩
ለእኔማ እናንተ ምስክሮች ልትሆኑኝ በእናንተ ልከ
በር ይገባ ነበር እኔ እንደ ኢምንትም ብሆን ሐዋር
ያት ሁሉ ከሠሩት ሥራ ካስተማሩት ትምህርት ያጐ
ደልኩባችሁ የለምና ።
የሐዋርያት ትምህርትማ በፍጹም ትዕግሥት በተአ ፲፪
ምራት ድንቅ ሥራ በመሥራት ሙት በማስነሣት
ተደረገላችሁ ። ምዕ ፲፪ ፭ ።
ላስቸግራችሁ ካለመምጣቴ ከዚህች በቀር ከምእመ ፲፫
ናን ሁሉ ያሳጣኋችሁ ያጐደልኩባችሁ ምንድር
ነው ? በደልህ ይህች ናት በሉኝ ። ምዕ ፲፩ ፱ ።
እነሆ ወደ እናንተ ልመጣ ስሰናዳ ይህ ሦስተኛዬ ነው ፤ ፲፬
ግን አልተሳካልኝም ገንዘባችሁን ያይደለ እናንተን

ንዋየክሙ እስመ ርቱዕ አበው ይዝግቡ ለውሉ
ዶሙ ወአኮ ውሉድ ለአዝማዲሆሙ ።
፲፭ ወአንሰ ምክዕቢተ አስተዋፃእኩ ወእሜጡ ሥጋየ
በእንተ ነፍስክሙ ወእመኒ ፈድፋደ አፍቀርኩክሙ
ርእስየ አፍቀርኩ ።
፲፮ ወአንሰ ኢያክበድኩ ላዕሌክሙ ወባሕቱ መስተመይነ
ከዊንየ ነሣእኩክሙ በጕሕሉት ።
፲፯ በኑ እንጋ ዘፈነውኩ ኀቤክሙ ወበኑ ዘተበገልኩ
ክሙ ።
፲፰ ናሁ አስተብቋዕክዎ ለቲቶ ወፈነውክዎ ለካልእ እኁነ
ምስሌሁ በኑ ዘገፍዐክሙ ቲቶ አኮኑ በውእቱ መን
ፈስ ዘይረውዕ በላዕሌሁ በቱ ሐርነ ወአሠረ ዚአሁ
ተለውነ ።
፲፱ ትትሔዘቡነሁ ከመ ንሕነ ንትዋቀሠክሙ ዘሂ ንነግር ፥
በቅድመ እግዚአብሔር በእንተ ክርስቶስ ንነግር
ወዝንቱሰ ኵሉ አኃዊነ ከመ ትትሐነፁ ።

፳ ወባሕቱ እፈርህ ለእመቦ ኢመ አመ መጻእኩ ወኢ
ረከብኩክሙ በከመ እፈቅድ ወአነሂ እከውነክሙ
ከመ ዘኢትፈቅዱ ወዮጊ ይከውን ውስቴትክሙ
ተዝኅሮ ወተቃንኦ ወተምዕዖ ወተሣልቆ አው ተሐ
ምዮ ወተሀውኮ ወአዕብዮ ልብ ።

፳፩ ዮጊ ካዕበ መጺእየ ኃቤክሙ የሐምመኒ እግዚአብ
ሔር በእንቲአክሙ ወእላህዎሙ ለብዙኃን እለ
አበሱ ወኢነስሑ በእንተ ኀሣሮሙ ወምርዓቶሙ
ወዝሙቶሙ ዘገብሩ ።

ምዕራፍ ፲ወ፫ ፤

፩ ወናሁ ሣልስየ ዝንቱ እንዘ እመጽእ ኀቤክሙ አኮኑ
በአፈ ክልኤቱ ወሠለስቱ ሰማዕት ይቀውም ኵሉ
ነገር ።
፪ ወአቀደምኩ ነጊረ እምትካት ወአቀድም ወእነግር
ዓዲ በከመ እቤለክሙ እንዘ ሀለውኩ በቀዳሚ
ከማሁ እንዘ ኢሀሎኩ በሣልስ እነግር ለእለ አበሱ
ቀዲሙ ወለባዕዳንሂ ከመ አመ መጻእኩ ኢይም
ሕክ እንከ ካዕበ ።
፫ እስመ ተኃሥሡ መከራሁ ለክርስቶስ ዘይነብብ በላ
ዕሌየ ውእቱ አልቦ ዘይሰአኖ በኀቤክሙ ዘእንበለ
ዳእሙ ኵሉ ዘይትከሀሎ ።
፬ እስመ ዘሐመ ወተሰቅለ በድካም ሕያው ውእቱ በኃ
ይለ እግዚአብሔር ፥ ወንሕነኒ ንደክም ምስሌሁ ወነ
ሐዩሂ ምስሌሁ በኃይለ እግዚአብሔር በእንቲአክሙ።

፭ ወርእሰክሙ አመክሩ ለእመ ሀለውክሙ በሃይማኖት
ወርእሰክሙ ሕቱ ለእመቦ ዘኢተአምሩ ለሊክሙ
ወኢትጤይቁ ከመ ሀሎ ክርስቶስ ምስሌክሙ ወለእ
መሰ ኢኮነ ከመዝ ምኑናን አንትሙ ።

አሻለሁና ልጆች ለወላጆቻቸው ያይደለ አባቶች
ለልጆቻቸው ገንዘብ ሊያኖሩ ይገባልና ። ምዕ ፲፫ ፩።
እኔ ዕጽፍ ድርብ አወጣጣሁ ስለሕይወታችሁም ሕይ ፲፭
ወቴን አሳልፌ እሰጣለሁ እናንተን እጅግ ብወዳች
ሁም ራሴን መውደዴ ነው ። ፊልጵ ፱ ፲፮ ።
እኔ አላስቸገርኋችሁም ፥ ነገር ግን ብልህ ሆኜ በጥበብ ፲፮
ገንዘብ አደረግኋችሁ ።
በውኑ ወደ እናንተ የላክሁት መልእክት አለን? ፲፯
ወይስ የቀማኋችሁ አለን? ።
እነሆ ቲቶን ማለድኩት ከርሱም ጋር ሌላውን ወን ፲፰
ድማችንን ላክሁት ፥ በውኑ ቲቶ የበደላችሁ በደል
አለን? ቲቶ በተቃኘበት መንፈስ የተቃኘን እሱ በሄደ
በት ፍለጋ የሄድን አይደለንም ። ምዕ ፰ ፯። ፲፮ ፲፰።
እኛስ እንደምንወቅሣችሁ ታስባላችሁን? በእግዚአ ፲፱
ብሔር ፊት የምንናገረውንም በክርስቶስ ፊት እንና
ገራለን፡ ወንድሞቻችን ይህ ሁሉ ግን እናንተ ትፀኑ
ዘንድ ነው ።
ነገር ግን ወደ እናንተ መጥቼ እንደምወደው ሆና ፳
ችሁ ያላገኘኋችሁ እንደሆን፡ እኔም እንደማትወዱት
እሆንባችኋለሁ ፥ ወይም በመካከላችሁ ክ'ራት መቀና
ናት መበሳጨት መዘባበት ወይም መተማማት መታ
ወክ ልብን ማሳበጥ ይኖር ይሆናል ብዬ እፈራለሁ ።
ምዕ ፲ ፥ ፪ ። ፩ ቆሮ ፬ ፥ ፮ ።
ወይም እንደገና ወደ እናንተ መጥቼ እግዚአብሔር ፳፩
ያሳዝነኝ ይሆናል በድለው ስለ ጕስቍልናቸው ስለ
መዳራታቸው ስለሚሠሩት ዝሙታቸው ንስሐ ያል
ገቡትን እቀጣ ይሆናል ። ምዕ ፪ ፥ ፩ ። ፲፫ ፥ ፪ ።

ምዕራፍ ፲፫ ፤

ወደ እናንተ ስመጣ እነሆ ይህ ሦስተኛዬ ነው ፥ ነገር ፩
ሁሉ በሁለት በሦስት ምስክር የሚፀና አይደለምን?።
ዘዳ ፲፱ ፥ ፲፭ ።
ጥንቱን አስቀድሜ ተናግሬአለሁ ፥ አሁንም አስቀ ፪
ድሜ እናገራለሁ ፥ ቀድሞ ከእናንተ ጋር ሳለሁ እንደ
ነገርኋችሁ እንዲሁ ሦስተኛ ሳልኖርም ቀድሞ በድ
ለው የነበሩትን ለሌሎችም ቢሆን በመጣሁ ጊዜ
ዳግመኛ እንዳልራራ ለሦስተኛ ጊዜ እናገራለሁ ።
በእኔ አድሮ የሚያስተምር የክርስቶስን መከራ ትሻ ፫
ላችሁና ፥ እሱ በእናንተ ዘንድ የሚቻለው ነው እንጂ
ሁሉ የሚሳነው የለም ።
ደክሞ የታመመ የተሰቀለ እርሱ በእግዚአብሔር ፬
ኃይል ሕያው ነውና ፥ እኛም ስለ እናንተ አብረነው
እንደክማለን ፥ በእግዚአብሔር ኃይልም አብረነው
እንነሣለን ። ፊልጵ ፪ ፥ ፮ - ፰ ።
በሃይማኖት እንዳላችሁ ራሳችሁን መርምሩ ፥ ክርስ ፭
ቶስ ከእናንተ ጋር እንዳለ ራሳችሁ አታውቁ አት
ረዱ እንደሆነ ራሳችሁን መርምሩ ፥ እንዲህ ካልሆነ
ግን እናንተ የተናቃችሁ ናችሁ ። ፩ ቆሮ ፲፩ ፥ ፳፰ ።

## ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ፪ ።

፮ ወእትአመን አንሰ ታእምሩ ከመ ኢኮነ ምኑናነ ንሕነኒ ።

፯ ወንጼሊ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ኢይግበር እኩየ ላዕሌክሙ ወኢ ምንተኒ ወአኮሰ ከመ ኅሩያነ ንኩን አላ ዳእሙ ከመ አንትሙ ሠናየ ትግበሩ ወንሕነሰ ከመ ምኑናን ።

፰ እስመ ኢንክል ወኢአ እምጽድቅ ዘእንበለ ዳእሙ በጽድቅ ።

፱ ወእትፌሣሕ ሶበ ንሕነ ነሐምም ከመ አንትሙ ትጽንዑ ወትትፈሥሑ ወዝ ውእቱ ጸሎትነ ከመ አንትሙ ታርትዑ ልበክሙ ።

፲ በእንተዝ ዘንተ እጽሕፍ ለክሙ እንዘ ኢሀለውኩ ኀቤክሙ ከመ አመ መጻእኩ ምቱረ ኢይግበር በላዕሌክሙ ከመ ዘሥልጣንበ በዘአኮነኒ እግዚአብሔር ለሐኒፅ ወአኮ ለነሢት ።

፲፩ ተፈሥሑ እንከሰ አኀዊነ አጥብዑ ወተዐገሡ ወተሰነአዉ ወአምላከ ሰላም ወፍቅር የሀሉ ምስሌክሙ።

፲፪ ተአምኁ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት ፡ አምኁክሙ ኵሎሙ ቅዱሳን ።

፲፫ ጸጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወፍቅረ እግዚአብሔር ወሱታፌ መንፈስ ቅዱስ የሃሉ ምስለ ኵልክሙ አሜን ።

ተፈጸመት መልእክት ዳግሚት ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ወተጽሕፈት በፊልጵስዩስ ዘመቄዶንያ ወተፈነወት በእደ ቲቶ ወሉቃስ ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን ።

## ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ፪ ።

እኛም ብንሆን የተናቅን እንዳይደለን ልታውቁ እኔ ፮
እምናለሁ ።
ምንም ክፉ ነገር እንዳያደርጓችሁ ወደ እግዚአብሔር ፯
እንጸልያለን ፡ እኛ የከበርን ልንሆን አይደለም እና
ንተ መልካም ነገር እንድታደርጉ ብቻ ነው እንጂ ፡
እኛ ግን እንደተናቁ ሰዎች ነን ።
በእውነት ፀንተን እንኖራለን እንጂ ፡ ከእውነት መው ፰
ጣት አንችልምና ።
እኛ መከራ በምንቀበልበት ጊዜ ደስ ይለኛል ፡ እና ፱
ንተም ደስ ብሏችሁ በሃይማኖት ትፀኑ ዘንድ ጸሎ
ታችን ይህ ነው ፡ እናንተ ልቡናችሁን ቀና ታደርጉ
ዘንድ ።
ስለዚህም ከእናንተ ዘንድ ሳልኖር ይህን ጻፍኩላ ፲
ችሁ ፡ ለማፍረስ ያይደለ ለማነፅ እግዚአብሔር በሾ
መኝ ገንዘብ ሥልጣን ያለኝ እንደ መሆኔ መጠን በመ
ጣሁ ጊዜ ቍርጥ ነገር እንዳላደርግባችሁ ። ምዕ፡ ፲
፰ ። ምዕ፡ ፲ ፲፩ ።
ወንድሞቻችን! እንግዲህስ ደስ ይበላችሁ ፡ ፅኑ ታገሡ ፲፩
አንድ ሁኑ፡ የሰላምና የፍቅር አምላክ ከእናንተ ጋር
ይኑር ። ፊል ፩ ፡ ፬ ። ሮሜ ፳ ፡ ፴፫ ።
ክብር ባላት ሰላምታ እርስ በርሳችሁ ሰላም ተባባሉ ፲፪
ቅዱሳን ሁሉ እንዴት ናችሁ ብለዋችኋል ። ፩ ቆሮ
፲፮ ፡ ፳ ።
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፡ የእግዚአብሔር ፲፫
አብ ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ከሁላችሁ ጋር
ይሁን ። አሜን ።

የመቄዶንያ ክፍል በምትሆን በፊልጵስዩስ ተጽፋ በቲቶና በሉቃስ እጅ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከችው ሁለተኛይቱ መልእክት ተፈጸመች ።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ፡ አሜን ።